# የኔ ፡ ጋሻ



ከክፍሌ አቡቸር (ሻምበል)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# የኔ ጋሻ

ከክፍሌ አቦቸር (መ. አ.)

አዲስ አበባ 1978

# መታሰቢያነቷ

ፍጹም በሆነ የአብዮታዊ እናት ሃገር ፍቅር ለአብዮታዊት እናት አገር መጠበቅ፤ አቻ በማይገኝለት የሕዝብ ወገንነትና አለኝታን ለሕዝብ መብትና ነፃነት እምከበር ከፍልሚያው የመጀመሪያ ረድፍ ላይ ተሰልፈው ለሚገኙ፤ ሕይወታቸውን ቤዛ አድርገው ላለፉና አካላቸውን ላጐደሉ ውድ አብዮታዊ ጦር አባላት እንዲሁም በተመሳሳይ ሕዝባዊ ዓላማ ለአብዮታችን ድል ማድረግ በትግል ሜዳ ለወደቁ እውነተኛ የሕዝብ ወዳጆችና፤ ለመላው የዓለም ሕዝብ ሰላምና ነፃነት የሚታገሉ ሃቀኛ ሁሉ «የኔ - ጋሻ» መታሰቢያቸው ትሁን።

## ግጥም

«ከውጭው ዓለም ነባራዊ ዕይታና ከውስጥ
ሕይወት ሚስጥራዊ ዕውነታ ጋር ተፋጦ -
ተፋልጦ የሚባዘት የሕሊና ዳኝነት ውሳኔ ረቂቅ
የስነ - ቃል ልቃቂት ነው»

# ማውጫ


መግቢያ ....... 5
ታሪክ ብቻ (1977 ሕያውነት ....... 8
እኔስ ቃል የለኝም (1977 - አድናቆት) ....... 10
ሃሳብ እሹሩሩ (1965 - ትዕግሥት) ....... 18
ለመጨረሻው ፍርድ (1974 - ዕውነት) ....... 23
ይልቅ ገለል (1967 - ቁጣ) ....... 26
ጀግናው ጀግና ጠራ (1974 - የታሪክ ቅርስ) ....... 27
እኔ ምን አውቄ (1977 - ፀባይ) ....... 35
መኖሩ ከፋ እንጂ (1975 - ውበትና ልግመት) ....... 37
ሺ - ጊዜ ቢሞቱ (1975 - ዐላማ) ....... 45
በጸታዬ አትፈትነኝ (1976 - እኩልነት) ....... 49
ትዝታ (1977 - ትላንት) ....... 55
የውል ስም ሆነና (1968 - ልዩነት) ....... 58
ቼቼ - ሰንጋው መዘዜ (1973 - ሃሳብ) ....... 62
የሞተማ - ሞተ (1965 - ቁጭት) ....... 78
ማን ይደፍረው ነበር (1965 - ይዘት) ....... 85
«ወይ - ዕዳ» (1976 - ገጠመኝ) ....... 89
እናት - ሃገር (1974 - ዜግነት). ....... 92
የደሜ - ደም - መላሽ (1967 - አመጽ) ....... 99
የኔ ጋሻ (1976 - መስዋዕትነት) ....... 101

ያን ዕለት ሞት ይሙት (1974 - ፍጻሜ) .......... 112
ልቤ - ከእኔው ጽና (1967 - ወዳጅና ጠላት) .......... 120
እንዲህ ኖሯል? (1975 - ተፈጥሮ) .......... 122
ቁርጥ አቋም ነው (1978 - ግልጽነት) .......... 128
ሞስኮቫ (1975 - እንግድነት) .......... 129
ቃል - ገባሁልሽ (1976 - የመጨረሻ ቃል) .......... 135
ምስጋና .......... 137

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# መግቢያ

በታሪክ ዓይን የታሪክ ዕውነታ እንደ መሬት ስበት ሕግ ብርቱና የማይገታ ሂደት ነው።

የሥርዓት መገርሰስና የሥርዓት መገንባት የሸፍጠኞች መድረክ መደብዘዝና የትክክለኛ ፍርድ ሰገነት መድመቅ የትምክህተኞች ክንድ መላምና የቅን ሰዎች ሃቅ ማየል የግፈኞች ሕልውና መክሰምና የተጨቋኝ ዜጎች ሕየት መለምለም ከዚሁ የታሪክ ዕውነታ ሕግ ማህደር የተገኘ ዛሬም ነገም ምን ጊዜም የሚኖር ነው።

ዛሬ በእናት ምድራችን ላይ የሚታየው የሥርዓተ ማኅበር ሹም ሽርና የሚደረገው ወሳኝ የመደብ ፍልሚያ የዚሁ ታሪካዊ ዕውነታ ነፀብራቅ ዓይነተኛ ገጽታ ነው።

የሚገርመውና የሚያሳዝነው ግን የአድኅሮት ኃይላት በተግባር ከሚታየው ከዚህ ታሪካዊ ሃቅ ግንዛቤ ማግኘት ያለመቻላቸውና ኢምንት ሰውነታቸውን ለታላቁ የታሪክ ሕግ ማስገዛት ያለመፈለጋቸው ነው።

እንደ ኢንግልስ አባባል «ታሪክ ከግለሰቦች ምኞትና ፍላጐት ውጭ ነው»።..... በመሆኑም ቀናት - ከሣምንታት ወራት - ከዓመታትት ተባዝተው የሸመኑት «ታሪክ» በብዙኃን ሕዝብ ደምና ሕይወት ለብዙኃን ሕዝብ ምኞትና ፍላጐት ተገዥነቱን ካረጋገጠ አያሌ ዘመናት ተቆጥረዋል።

ወደፊትም የየቤቱ - የየሀገሩ - እና የየአህጉሩ ሕዝብ የሰላም የነፃነትና የብልጽግና፥ ሕይወት ፍላጐት፥ አንድ ዘመን - አንድ ቀን የሁሉም ዓለም ዜጎች የጋራ ዓርማና ማዕከላዊ ቋንቋ እንደሚሆን ከደረስንበት ዘመን ታሪካዊ ዕይታ አኳያ ዕውነታውን መተንበይ አያስቸግርም።

ይህች በ «የኔ - ጋሻ» ስያሜ ለአንባቢያን የቀረበችው የደራሲው የመጀመሪያ የግጥም ስብስብ መጽሐፍ የተነሣችውም ከዚሁ ታሪካዊ ሃቅ ነው።

የግፈኞች ሥርዓት «ክብረ - ስብዕናውን» የገፋው የስግብግቦች መዳፍ «ጥሪት - ገበናውን» ያስከፋው.....

«ኧረ ያገር ያለህ - አገር ለኔ አልሆነኝ

ኧረ የሰው ያለህ - ሰው መሆን መረረኝ

በላይ ቤት አልሠራሁ - በሥር አልተመቸኝ»

ሲል ዕለተ - ልደቱን የረገመውን ባክኖ መና «የኔ - ጋሻ» በዓይነ ሕሊናዋ ማስታወስ ብቻ ሳሆይ የዚህን የአገር ቋንቋ ተናጋሪ የአገር ብሶት መስካሪ፥ የቅርብ ሕይወት «እማኝ» በማድረግ ነው።

«የኔ - ጋሻ» ያለፈው አስከፊ ሥርዓት በመላው የሀገሪቱ ጭቁን ዜጎች ሰብዓዊ ሕይወት ላይ ያደርስ የነበረውን «ክብረ - ነክ» ድርጊት መመልከት ብቻ ሳይሆን የመከራው ተጋሪም ስለነበረች የወቅቱን ግፍ «ገጸ - ምስል» በታፈነ አንደበቷ መዝግባ በታሸገው መህደሯ አካታ የታሪክ ዕውነታ ሕግ በቀደደው ሁለንተናዊ ተነፃነት መድረክ ላይ ቆማ የትላንቱን ለ «ዛሬ» ለመተረክ የዛሬውን ለ «ነገ» ለማቆየት መልካም ዕድል አግኝታለች።

በ «የኔ - ጋሻ» ውስጥ የተካተቱት ግጥሞች የታሪክ ምስክርነታቸውን የሚጀምሩት ከ1965 ጀምሮ ሲሆን ከውቅያኖስ - ከሰፋ የአያሌ ዘመናት ውስብስብ የአስከፊ ሕይወት ትግልና - እንደ ጨረቃ ከደመቀ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የድል ታሪክ የጨለፈችውን -

የሰፊውን ሕዝብ የመከራ ሕይወት ገጽታና የበቃኝ አመጽ እንጉርጉሮ የቃኙ......

የአዲሱን ሥርዓት እውነተኛ የሰው ልጆች የነፃነትና የሠላም ድል ስምረት ጅምር ትግልና፥ በተከፈለው ሁለንተናዊ መስዋዕትነት የተገኙትን ታላላቅ ድሎች በአንኳር በአንኳሩ ያማትሩ.......

ወላዊና ግላዊ ሕይወት ዕለታዊ ገጠመኞችን የሰው ልጆችን ሕይወት ምስጢራዊ ስሜት በወፍ በረር እይዳሰሱ የስነ ቃል

ግጥምጥሞሽን ያካተተች ሲሆን በተለይም የዚህን ትውልድ ሕዝባዊ ዓላማ ጽናትና የአብዮታዊ እናት ሀገር ፍቅር ስሜት በማይፋታ ቃል ኪዳን ያረገገጠችበት ሰነድ ይዛ ቀርባለች።

አዲስ አበባ

1978

# ታሪክ ብቻ (1977 ሕያውነት

የጠዋት - የጥንት - ስር
ሕግ ሆነና የሂደት ድር
በሌት ኮከብ በቀን ጀንበር
ቀን ሲቀነስ ቀን ሲደመር
ዘመን ደርሶ ዘመን ያልፋል
ሰው ይሞታል።
 በዚች ዓለም በዚች ምድር
 በውስብስብ ሕይወት ሚስጢር
ያ - ቢደሰት ያ - ቢከፋ
ያ - ቢ ‹ቢገፍ - ያ ቢ ‹ገፋ›
ያ - ቢጐብዝ - ያ ቢደክም
ቀን ቢፈካ - ሌት ቢጨልም
ወደብ አልባ - የዑደት ጥግ
ሂደት እንጂ - የታሪክ ሕግ

 በዚች ምድር የዚች ዓለም
 ዛሬ ቢኖር ነገ የለም።
 ታታሪ - ወይ - የአባያ

የሊቅ - ደቃት ድንቅ ሙያ
የደግነት ወይም የክፋት
የጀግንነት ወይ የክፍርሃት
ወይ የመጥፎ ወይ የጥሩ
ኗሪ ማህደር ምስከሩ
ለያንዳንዱ ቤት መነጽር
የስተጀርባው ዕልፈት ምስጢር
ትላንትና ዛሬም ነገርም
የሚኖረው ለምን ጊዜም
የክንውን ድርሰት - ሰቅ
«ታሪክ» ብቻ ሕያው ሰንደቅ።
ከዚህ ሌላ ከዚህ በቀር
በጥላቻ ወይ በፍቅር
አሊያም በፌዝ ወይም በምር
በቆይታው..... የሚጸና
ምንስ ነገር ምን አለና?
በዚች ዓለም በዚች ምድር
«ታሪክ» ብቻ ሕያው ነገር።

...............

..............................

................................................

# እኔስ ቃል የለኝም (1977 - አድናቆት)

ታጋይ ጓድ አልልህ.....
ገላጭ ቃሉ አነሰኝ
ሞትክን ሞት አልለው.....
ተራ - ሞቱ ታየኝ
ግን የአንተ ጀግነንት.....
የአገር ሞትህ ምስሉ
የምሽግ ሕይወትህ......
እንዴት ይባል ቃሉ?
የወንዝ የድንበር ልጅ......
ያገር ሰው ሰብስቤ
የቅርብ የሩቅ ወዳጅ
አጋር ሰው ደርቤ
ባጽፍ ወይ ባስቀርጽ
ግጥም ባስደረድር
ባስል ወይ ባዘምር.....
ብናገር ባስነግር
መቸ ተገኘ ቋንቋ.....
ለአንተ ውሎ ገድል

ተግባርከን የሚገልጽ.....
አንተን የሚወክል?
የሚስጢር ጓደኛ.....
የአንጀት ባልደረባው
የብረት ባርኔጣው.....
ኮዳና ጀበርናው
የአገር ሰማይ አገር......
የአገር ላዩ አየር......
የአገር ኬላው ባሕር.....
የደም ፍሳሽ በሩ
እንዴት እንደሆነ.....
የዚያ ሰው አዳሩ
ተናገር ጠብ - መንጃው.....
ተናገር ዝናሩ
አንተ ነህ ምስክር.....
አንተ ነህ አጋሩ።
የበረሃው ንዳድ......
አሸዋው ክምሩ
ኮረብታው ቋጥኙ......
ጅረት ተረተሩ
ተማለደኝ ዱሩ......

ተለመነኝ ጫካው
አበድረኝ ቋንቋ.....
ንገረኝ ተራራው
ተናገር ማዕበሉ......
ረሞጫ አመዳዩ
ተናገር አሞራው.....
ተናገር ሰማዩ
የሚስጢር ጓደኛህ......
ታሪክ ስንክሳሩ
ምን ተብሎ ይፃፍ......
ምን ይባል ምግባሩ?
የአዲስ ሕይወት ብስራት.....
ተስፋ ያለሙብሽ
ደም ሰጥቶ ደም ወስዶ....
ውሎ ያደረብሽ
«እምቢኝ» ባለ ወኔ....
.....ለአፈር ጥሪት ክብርሽ
ጀግና ልጅ ተወልዶ.....
ጀግና የቀረብሽ
የታሪኩ ግኝት.....
......ማገር ድምድማቱ

የሕይወቱ ሰንደቅ.....

....የሙት አካል ቤቱ

አንቺ ስለሆንሽ.....

.....ንገሪኝ ምሽጉ

ምን ተብሎ ይፃፍ.....

....የዚህ ጀግና ወጉ?

የጀግንነት ክራር.....

.....የትዝታ ቤቱ

የእህል ቁጭት ዜማ.....

....መሲንቆው ዋሽንቱ

ዓላማውን ጽናት......

.....የሕይውቱን ታዛቢ

ስቃይ መከራውን....

.....ታሪኩን መዝጋቢ

የሚስጢር ማህደሩ.....

.....የቀን የሌት ጓዱ

የልብ ወዳጅ ጋሻው.....

......የድል ግኝት ገዱ

አንቺ በመሆንሽ......

......የኃዘን ዳስ የሰርጉ

አበድሩኝ ቋንቋ.....

.....ቃል ስጭኝ ምሽጉ
ምን ተብሎ ይፃፍ....
.....የጀግናሽ ድል ወጉ?
አበድሩኝ ቋንቋ.....
.....መቼም የማልከፍለው
የማልቀጣበት......
......የማልያዝ በዕዳው፡፡
ለአንድ «ሃገር» ለአንድ «ዕውቀት»
......ንፁህ ዜግነቱ
ቆራጥ ጀግንነቱ.....
.....ርህሩህ ደግነቱ
ለቅን ፍልሚያው ተግባር.....
.....ለሕዝባዊነቱ
የዚህ ጐበዝ ሕይወት.....
......የዚህ ጀግና ሞቱ
ምን ተብሎ ይፃፍ.....
......የታሪክ ዕውነቱ?
ለአንድ «እውነት» አንድ «ሕይወት».....
......ለድል ግብ ከማቅለም
ከሬት ምሬት መድረክ.....
.....ማር ዕንቁ ከማለም

«ወራት ቢለዋወጥ.....

......ሌት ይሁን ወይም ቀን

ለፈለገው ዓመት.....

.....ለፈለገው ዘመን

አፈር ልሁን ትቢያ......

......ስቃይ ምሳ ራቴ

ከግንባሬ ይዋል.....

.....ጥይት በደረቴ

ብቻ! «እናት - ሀገሬ»......

......ወገን ድል ይቀበል

የሕኝይወቴ ዕልፈት.....

......አዲስ ሕይወት ያብቅል»

ከማለት በስተቀር......

ምን ቃላት ተንፍሷል

ሚስቴ ወይም ቤቴ.....

......ልጆቼ ናፈቁኝ መች ቀን ብሎ ያውቃል?

እስካሁን ላለበት......

......ላገር ወገን ስቃይ

ሰልችቶት ወይ ደክሞት......

......ከፍቶት ያውቅ ይሆን ወይ?

ሰዎች ይህንን ሰው

ታዲያ ምን....... ልበለው?

በምን ቋንቋ ጽፌ......

......ምን ብዬ ልግለፀው

የርሱ ሕይወት ከኔ.....

......እንዴት ላስተያየው?

በደም ያስከረህ.....

.....የአጥንት አጥር በሩ

የአገር ክልል አድማስ.....

.....የአገር ሰማይ ክብሩ

እስቲ አሁን ነህና......

......የአገር ዳር ባህሩ

አበድረኝ ቋንቋ.....

.....ንገረኝ ድንበሩን።

እንዲያው በጥቅሉ......

......የወገን ድል አርማ

የሃገር መሃል - ዳሩ....

.....የሃገር ሕይወት ሻማ

የገጽታዬ ገጽ......

......ዋልታና ማገሩ

የማንነቴ ምን......

.....ሕሊናዬ ክብሩ

ካላልኩህ በስተቀር......

......ሁለንተ - ገላዬ

ጋሻ - መከታዬ......

....መመኪያ አለኝታዬ

የአንጀት ፍቅሬን ምሥጢር....

......የስሜቴን አንቀጽ

በምን ቋንቋ ጽፌ.....

......እንዴት ብዬ ልግለጽ?

በሀገር ባህል ቋንቋ.....

......በሃገር ሕይወት ምስጢር

የሕይወቴ ጋሻ.....

....የእናት ዓለም አጥር

ካልላኩህ በስተቀር......

.....በወሎ ስመ - ጥር

ታሪክ - ገድልህን......

.......የሚገልጽ የሚያሳይ

እኔስ ቃል የለኝም......

.....ቃል ለምድር ለሰማይ!!

## ሃሳብ እሹሩሩ (1965 - ትዕግሥት)

እልፉጭ...... አልጋጭ
ውል አግኝቶ..... አልቋጭ
ብሎኝ እንጂ አቅሜ
ፈር አጥቶ እንጂ ሕመሜ
ለይቶ እንጂ ልሳን
ገምቶ እንጂ ሚዛን
ጠንቶብኝ ሕመሙ
አስሮኝ እንጂ - ጣሙ
መሰንበት ደግዬ.....
......መቆየት መልካሙ
መች ያቅተኝ ነበር.....
......በእልህ መላተሙ?
እናማ..... ነገሩ
መች የወል አገሩ?
ወገን..... ከወገኑ
ዘመን..... ከዘመኑ
እስኪገጥም..... ቀኑ
ቀን ይግባ ቀን ይውጣ
ቀን ይለፍ ቀን ይምጣ

ብዬ እንጂ ማደሬ
በቀን ቀን መቁጠሬ
እናማ...... ነገሩ
መች የወል አገሩ?
　　　　እንዲያ.... እንዲያ.... መሆኑን
　　　　መች አጣሁ..... ሚስጥሩን።
ምኞት የአገር ዳሩ
እህል የአገር በሩ
እስቲ አይከፋምና.....
　　　　.....በቀን ቀን መቁጠሩ
እስኪሳብ.... ሃሳቤ
ልብ እስከሚል ልቤ
ችግር የአገር መሃል ችግር የአገር ዳሩ
እስኪበጠስ..... ስሩ
እምቢኝ አካል ገላ..... እምቢኝ አካል ገሩ
እሹሩሩ..... ሃሳብ..... እሹሩሩ..... ሩሩ
እሹሩሩ...... ገላ...... እሹሩሩ...... ሆዴ
እሹሩሩ..... ሃሳብ...... እሹሩሩ....... ክንዴ።
　　　　ይልቅ ጭልም ሕይወት.....
　　　　　　　　......ጥቅጥቅ ጭልም ተስፋ
　　　　እንዳይሆን የባሰ.....

.....እንዳይንሆን የከፋ

ያንን ትልቅ ግርዶሽ.....

......ያንን ትልቅ ዋርካ

ትንሽ ትንሽ ቀንጠስ......

.....ትንሽ ትንሽ ንካ።

ያ! ተራራ እንዲናድ.....

......ጥርጊያ መንገድ ቆንጥር

አንተም የድርሻህን.......

.....ትንሽ ትንሽ ቆፍር።

እሹሩሩ ሃሳብ..... እሹሩሩ......ሩሩ

እስቲ አይከፋምና...... በቀን ቀን መቁጠሩ።

ሰምቼ ሳልሰማ......

.....ጨለማውን ፀሐይ

የማውቀውን ሳላውቅ......

.......ያየሁትን ሳላይ

እኔነቴን በኔ.....

......እኔው መፈጠሬ

ይሁን ስል......ማደሬ

ይሁን ተብሎ እንጂ

......ያቅም ግብ ሆነና

መች አጥቼ ብለህ......

.......የውስጤን ገበና?
እግራም ተባልኩ እንጂ......
.......ሳያውቀው ያወቀኝ
መች ተራመድኩበት......
.....ካልኩት መች ወሰደኝ?
ምላስ እንደበቴን.....
......ቋንቋ መች ጐበኘው
መች ተናገርኩበት......
.......ልቤ እንደተመኘው?
ለጐረቤት ትፍስህት........
......ለዚያ ፀጋ ውሎ
«እድር» ሲል ኖረ እንጂ......
......የራስ ቤቱን ገሎ
መች ሳቀልኝ ጥርሴ......
.....የኔን ለኔ ብሎ?
እንደ አዋሉት ውሎ......
.......እንዳሉት ከማደር
ያሰሙትን ሰምቶ......
.......ሙቱን ከመገበር
ከመልቀም ከማፍሰስ......
.......ጆሮዬ ምን ሠርቷል

ያቆየኝ ምን አለ......
......ለኔ ያለው የታል?
ነፍሮ - ከመነኮር
«ችሎ - ማደር» በሉኝ
......እያለ ከመኖር
ሆዴ ምን ፈየደ?.....
......ምን ፈጠረ መላ
«እህህን» ወግ ብሎ.....
......ከመቃጠል ሌላ?
ቢያጣ ቢያገኝ ምኑም....
.....ክፉ ደግ የለየ
ዓይኔ ነው የኖረ.....
.....ያሻውን እያየ።
አለው ተባልኩ እንጂ......
.......መታያ ናሙና
ሁሉስ ቢሆን ለኔ.....
......መች የኔ ሆኑና?
እልህ ምሳ እራቱ......
......አካል ገላ ጽና።
እሽሩሩ ሃሳብ...... እሹሩሩ ገላ
ይልቅ መላ ፍጠር......

......መላ ፍጠር መላ!!

## ለመጨረሻው ፍርድ (1974 - ዕውነት)

«ጭነት ባይኖር ኖሮ..... ዶሮም ወደል ሲባል
ዝናብ ባይኖር ኖሮ..... ደረባም ቤት ሲባል
ቀውጢ ቀን ባይመጣ....... ፈሪም ጐበዝ ሲባል
ጉግስ ባይኖር ኖሮ....... በቅሎም ፈረስ ሲባል
እንክርዳድም ስንዴ...... ሐሠትም እውነት ሲባል
ይኖር ነበር እንጂ......ማነኛው ምን ይላል? »
ይሉ እንዲሉ አበው.......
የትኛው ተመክሮ...... የትኛው ሊዘ'ከር
አንዱ ባንዱ ታኮ...... ከመቀመጥ በቀር?
እንዲያው በደፈና..... እንዲሁ በደርዘን
ሚስጢር ሳይከሰት ቅንጣትም ሳይባክን
ሁሉም በዝም ዝም..... እንዲያው በሽፍንፍን
በለስላሳ ምላስ...... በጐሽ..... ይሁን ይሁን
ዝንተ ዓለም ለመኖር....... በታደለ ነበር።
ዳሩ መች ሆነና......
ጐርፍ ሲመጣ እንጂ...... ነጐድጓድ ሲነጉድ

የደረባ ምሥጢር..... የሚከተሰው ጉድ።

ጀግና ሲመጣ እንጂ..... የፈሪ ሞት ሞቱ

ሜዳው ገደል ሲሆን..... እዳሪው ሲቀጥን..... ሲጠቁር ቅላቱ።

ተግባር ሲመጣ እንጂ...... ማንነትን ወሳኝ

መፈተኛው መድረክ...... በሕሊና ሲናኝ።

ንጋት ሲመጣ እንጂ..... የጭለማ ሞቱ

ምርከ ከእንክርዳዱ....... የሚለይ ከቴልቱ

ሃቅ ሲመጣ እንጂ..... ሃቀኛ ሲፈለግ

የቀጣፊ ምሽግ...... ማንቁርት የሚሰነግ

ገንቢ ሲመአ እንጂ..... ሃቅ እውነት ሲለሰን

የአፍራሽ ፍርክርኩ....... ዕድሜ የሚወሰን።

ሁሉም በየተራው...... ሂደቱን ለጥቆ

ሁሉም በየቦታው....... ዕድገቱን ጠብቆ

መለየቱ አይቀርም....... መታየቱ አይቀርም.....

አንዱ ካንዱ ለቆ።

እንዲያ ባይሆን ኖሮ....... የታሪክ ሃቅ ዕውነት

እንዲያ ባይሆን ኖሮ...... የታሪክ ሕግ ዕድገት

የሰው ልጆች ሕይወት....... የተፈትሮ ቅምር

የዕለት በዕለት ተግባር...... የዘመናት ድምር

የሰው ልጆች ክብር...... የመኖር አርነት

በጨቋኞች ጡንቻ..... በግዞት ሰንሰለት

በዕብሪተኞች መዳፍ..... በወሽካቶች ምላስ
ሃቃቸው ተቀብሮ..... ይኖር ነበር ሲላስ።
የጉስቋሎች ሕይወት...... በዕብሪተኞች አምባ
ይኖር ነበር ኑሮ...... ዝንተ ዓለም ሲያነብ።

ግን ሳይሆን ቀረና
የዕብሪተኞች ዕብሪት...... የዘረፋ መና
የግለኞች ምስጢር..... የድብቅ ገበና
የብዙኃን ሕይወት...... የዕውነት ጐዳና
ሁሉም በታሪክ ሕግ...... ከዕድገት ጋር ሆነና

የንጹሃን ዕውነት...... የግፈኞች ፍዳ
በትንቅንቅ ጉዞ...... በሞት ሽረት ሜዳ
ሁሉም በየመልኩ....... ከነ - ዶሴው ቆሟል
ለመጨረሻው ፍርድ...... ከሐቅ ፊት ቀርቧል።

...........

..............................

..................................................

......................................................................

## ይልቅ ገለል (1967 - ቁጣ)

እሳት እንጂ ቋያ ሰደድ
በልቤ እልፍኝ የሚነድ
ሕይወት እንጂ የሕዝብ ዕምነት
የአገር ፍቅር የአገር ዕውነት
ፍቅር እንጂ ቀና መንገድ
የወል ሕይወት የወል አፀድ
የታሪክ ውል ትግል ጽናት
ቀንዲል እንጂ የድል ንጋት
ከእንግዲህ መች ግዞት ለኔ
ገባርነት - በራብ ጐኔ?
ይሄ ንጋት መች ይጨልም
ቆሌዬ መች አክሊል ያልም?
ይልቅ...... ይኸው
ቃሌን ስማ....... ክንዴን እየው
ትግሌ ከትግልህ ላይገናኝ
ግቤ ለግብህ ላይጐዳኝ
ሃቂ ከሽፍትህ ላይቀናጅ
ወዜ ከገድህ ላይወዳጅ
ከይሁዳ የዘር ሀረግ

ላንማዘዝ...... ላንዳረግ
ከእምነድህ የድመ አስኳል
ላንኳኳን...... ላንኳኳል
ተነፋፍቀን... ላንሳሳም
ቋንቋ ከግብር....... ላንጣጣም
ይልቅ ገለ ከመንገዴ..... ከመስመሬ አትዳፋ
ይህን ማዕበል አትጋፋ!

.........

...........................

..............................................

...................................................................

.............................................................................................

## <u>ጀግናው ጀግና ጠራ (1974 - የታሪክ ቅርስ)</u>

ጊዜ የማይሽረው...... ታሪክ የማይስተው
የጀብደኞች ጩኸት...... ዕብሪት የማይፍቀው
የደም ፈሳሽ ውጤት..... የድል መሠረቱ
የእናት ሀገር ፍቅር...... ነበልባል ስሜቱ

የጅግግንነት ወኔው..... ኮስታራው ሃሞቱ

የወጣበት ዳገት የዋለበት ሜዳ ጉራንጉር መንገዱ

የተፋለመበት ጥሎ የወደቀበት ቃጠሎ ንዳዱ

ጥይቱን በደረት ታንኩን በጎራዴ የገመሰው ክንዱ

ባህር ውቅያኖስ....... አገር ድንበር ዞሮ

ወንዙን - ተረተሩን...... አድማስ - ሰማይ በሮ

ድቅድቁን ጨለማ....... ተራራውን ንዶ

የተዘጋ መስኮት..... ሕንጻውን በርግዶ

ጀግና ከቆመበት....... ከሄደበት ውሎ

ከለበሰው ሸማ....... ከሄደበት ውሎ

ከለበሰው ሸማ...... ውበት ተመሳስሎ

ከሚበላው እህል...... እህል ሆኖ በስሎ

ከሚጠጣው ውሃ...... ፍሳሽ ተቀላቅሎ

የጀግናን ደም ስሜት..... ወኔውን ፈንቅሎ

የጀግናን ሰውነት...... ሃሳቡን በርቅሶ

የደም ሥር መንገዱን...... ሕሊናውን ጥሶ።

የአባቶች አደራ

የጀግኖች ደም ጐራ

መሰል ባለወኔ መሰል የአካል ክፋይ...... መሰል ጀግና ጠራ!

ብሎ ተማጸነ ታሪኬን አደራ! - ታሪኬን - አደራ!!

«የተፋለምኩለት ጥዬ የወደኩለት....... የእናት አገር ክብር

የአንድነት ታሪኩ የነጻነት ውሉ...... ከቶ እንዳይደፈር።
ምንጊዜም እንዲኖር...... በድል መድረክ ጉራ
ታሪኬን ተረክበህ..... ዓርማዬን አንግበህ..... ተነስ ተሰማራ!»
እያለ ተጣራ!
የጀግኖች ደም አጥንት የጀግኖች ደም ጉራ!!
«ትውልድ ለሚወርሰው...... ነፃነት ዘምቼ
ለአንድነት ዘር ሐረግ...... ቆስዬ ደምቼ
ታሪክ ለሚያወሳው......አኩሪ ታሪክ ሞቼ
        በደም ቀለም ጽፌ....... ያኖርኩት ሃቅ እውነት
        በአጥንቴ ክስካሽ...... ያበበው ነፃነት
        በሕይወት ዕልፈት....... ያሰርኩት አንድነት
አገር...... አድማስ...... ሰማይ
አገር....... ዙሪያ..... ፀሐይ
አገር....... ዙሪያ..... መንደር
የአገር...... ባህል....... ዕምነት
የአገር...... ዙሪያ...... ሕይወት
የአንድነት..... ዙሪያ..... ሐውልት።
ያ! የታሪክ አምባ...... የአኩሪ ገድል መንደር
የነ - ዘራይ ድረስ..... የዮሐንስ አገር
ያ! የጀግና ሰፈር..... የመቅደላው አፈር
የነ - ቴዎድሮስ...... የእናት አገር ፍቅር

ያ! የጀግና ሰፈር....... የታጋዮች ደብር
ያ! ምኒልክ መድረክ..... የነ - አሉላ ባህር
ያ! የታሪክ አምባ....... የጀግኖች ድል አጥር
በታሪክ እጣቢ ኋላ እንዳይደፈር
የአንድነት ማገሩ እንዳይሰነጠር»
እያለ ተቆጣ! ብሎ ተናገረ
ለእናት አገር ፍቅር ወድቆ የነበረ።
ብሎ ተናገረ! ብሎ ተማጸነ! ታሪኬን አደራ!
የጀግኖች ደም ሕይወት..... የጀግኖች ደም ጐራ!
መሰል ባለወኔ...... መሰል የአካል ክፋይ..... መሰል ጀግና ጠራ!!
መቅደላ ላይ ያለው..... ማይጨው ላይ የቀረው
አድዋ መተማ...... ወልወል የወደቀው
ዶጋሊ ጉንዲት...... ዶሎ ላይ የተኛው
ቆራሄና ሽሬ...... ጉራዕ የተሰዋው
በኦጋዴን ምድር....... በትግል ያለፈው።

ምሥራቅ ድንበሩ ላይ...... ጋሻ ሆኖ ያ'ለው
ደቡብ ድንበሩ ላይ........ ኃውልት ሆኖ ያ'ለው
ሰሜን ድንበሩ ላይ........ ሰንደቅ ሆኖ ያ'ለው
ምዕራብ ድንበሩ ላይ...... አጥር ሆኖ ያ'ለው
የጀግኖች ደም አጥንት...... የጀግኖች ደም ጐራ
ውድ እናት አገሬን...... ኢትዮጵያን አደራ!

ኢትዮጵያን አደራ!....... ኢትዮጵያን አደራ!»
እያለ ተጣራ
ጀግናው ጀግና ጠራ ጀግናው ጀግናን መራ!!
 የድል ሲቃ! ይዞት
 የድል ሽታ! ሸቶት
 የአገር ፍቅር ሞቱ...... ስሜቱ አምጾ
 የጀግናው ጀግንነት....... ደም አጽሙ ተናውጾ
«ይኸው ዛሬ ደርሶ
አጽሜ..... ታሪክ ለብሶ
በኖረበት...... አገር
በአለፈበት..... ምድር
 የደም ሕይወት እያ'ለ....... ታሪክ ምስክሩ
 የዘር ሐረግ ቆሞ...... ታሪክ መዘክሩ
 ሐቅ እውነት ተጽፎ...... የታሪክ ምግባሩ
 የእናት ሃገ ዋልታ...... እያ'ለ ማገሩ፥
 የታሪክ ቅርስ እምነት...... እያ'ለ ማህደሩ
 ጀግና ጠንቀቅ በል...... እንዳይጣስ በሩ
 እንዳይጐድፍ...... ክብሩ
የእናት ሀገር እውነት..... ኢምንት ላይሰእይፍ
የሐቅ ዕምነቷ ድል...... ቅንጣት ላይዛነፍ
ጀግኖች ማዕከል...... የወላዶች ማህፀን

ጀግና ከማበርከት....... ከማፍራት ሳይመከን
የታጋዮች ቁጥር...... ታሪክ ላይመነምን
ባህረ መዝገቧ...... በጠባቦች ምኞት ቅዠት ላይወሰን
በውዳሴ ከንቱ..... ጋለበ ነፈሰ
በውዳሴ ከንቱ..... ጉራ ተነፈሰ
በቀቢጸ ተስፋ...... ጉራ ተነፈሰ
በእርግጥ......

በአኩሪ ጀግኖች መድረክ...... የአገር ፍቅር አንጀት
የትውልድ አተላ!...... የታሪክ ቅራሪ ያሳዝናል ማየት!
ውድ እናት አገሬን...... «ኢትዮጵያዬን» ብለው በወደቁት ምድር
መስማት ያናድዳል....... ማየት ያሳዝናል..... ከሃዲ ሲፈጠር!

እና........

«ታሪክ...... ታሪክ..... ስሎ
ሃቅ...... እውነት....... አብቅሎ
ጀግና...... ጀግና....... አፍርቶ
ትግል........ ለድል ወጥቶ
ጀግና...... ለድል...... ደምቶ
ጀግና........ ለድል....... ሞቶ
ሐቅ...... እውነት...... አብርቶ
ሐቅ...... እውነት....... አጥርቶ
በየድል....... ጐራው

በየድሉ...... አውድማው
ጉሮ ወሸባዬ...... የደስ ደስ ሲዘመር
እንዲያ...... እንዲያ...... ጀግናዬ.....
እንዲያ ሲል ግዳዬ! ተብሎ ሲነገር
እንደ ሙዳ ሥጋ...... ከሃዲ ሲመተር
ዘራፍ ጃሎ መገን! የጀግና ልጅ ጀግና! ተብሎ ሲፎከር!!
ከአላየሁኝ....... በቀር
ከአልሰማሁኝ....... በቀር
ብዬ አልናገርም....... ታሪኬ እንዲሁ ነበር
ምን ዕረፍት አለና...... ተደፍራ እናት ሃገር?
ስለዚህ -
ማየት እምነቴ ነው...... የድል ምላሽ መሌን
መስማት ምኞቴ ነው...... የአደራ ቃል ውሌን»
ብሎ ተናገረ...... የጀግኖች ደም ጐራ
ብሎ ተማጸነ..... ታሪኬን አደራ
መሰል ባለወኔ..... መሰል የአካል ክፋይ...... መሰል ጀግና ጠራ!
ጀግና ጀግናን ጠራ! ጀግናው ጀግናን መራ!!
«የደም ጥሪ ቃል ቃልክን...... ጩኸትን ሰምቼ
የአኩሪ ታሪክ ሞትክን...... ዓርማህን አንስቼ
በትኩስ አዕምሮ በአዲስ አፍላ ጉልበት
በብሩህ ሕሊና በአዲስ ሥርዓት ስሜት

በነአደ ስሜት በአገር ፍቅር ዕሳት
በወሳኝ ድል ጉዞ በሐቅ ዕምነት ብቃት
ከዘመኑ ዕብሪት ከወራሪ ጥቃት
ውድ እናት ሀገሬ በድል ልጠብቃት።
ቃል እገባለሁኝ ጥዬ ልወድቅላት
ብለህ በለኝና
ስጋቴን ልተወው በድል ታሪክ ልጽና!»
ብሎ ተማፀነ...... የጀግኖች ደም ጐራ
መሰል ባለወኔ..... መሰል የአካል ክፋይ......
ጀግናው ጀግና ጠራ..... ጀግናው ጀግና መራ!!

.............

...................................

.....................................................

.......................................................................

...........................................................................................

## እኔ ምን አውቄ (1977 - ፀባይ)

የናቀኝ ተንቆ - የገፋኝ ሲገፋ
ያስለቀሰኝ ሲያለቅስ - ያስከፋኝ ሲከፋ
«ግዳዬ» ሲሰምር - ሲባል ጉሮ ወሸባ
ጉንጉን በአንገቱ ላይ - ሲበተን አበባ
ያላሰብኩት ሲደርስ ዕልምቴ ሲመታ
ዕሳት...... ስለ..... ሆኖ ቋጠሮ ሲፈታ
ፍልቅልቅ ስሜቴ ውስጠ - ሕይወቴን ሲገልጽ
በሁለንተናዬ በአካላቴ ሲሰርጽ
ምኞቴ ሲሰምር - ሃሳቤ ሲሳካ
«ፈገግ» ይላል «ጥርሴ»...... ደስ ብሎት ሲረካ።
ሆዴን ነገር ዘልቆት - አዝኜ ሲከፋኝ
ቃጠሎ እንፋሎቱ - እምቅታው ሲገፋኝ
የአካል አንደበት - የአቅሜ አቅም ሲገባኝ
የማደርገው ሳጣ የምለው ሲጠፋኝ
ድብን...... እርር...... ኩምትር..... ቆሽቴ ክስል ሲል
«ፈገግ» ይላል «ጥርሴ» ደስ ያለው ይመስል።
የአካሌ አንድ አካል - የፊቴ ገጽታ
የስሜቴ ገላጭ የጥርሴ ብልጭታ
ፍንድቅድቅ አዳሬን ውሎ ደስታዬን

ድንቅ ሕይወቴን ብቻ ሣይሆን እርካታዬን
ውስጥ አንጀቴ ሲነድ ሾቆ ሲንገረገብ
ሲከፋኝ መሣቄም ዕውቅ ሆኖ ይመዘገብ።
        ተፈጥሮ ሆነና - አብሮኝ ስንባች አመል
        የራስ ጉያ ጠባይ የራስ ስሜት በቀል
ስሜት ሲተራመስ - ስሜት ሲደባለቅ
ሕግጋት ሲጣሉ - ሣቅ መስመሩን ሲለቅ
«ሕመም» ይሁን «ጤና» እኔ ምን ዐውቄ?
የገረመኝ ቢኖር ሲከፋኝ መሣቄ።
ሲያዝኑም...... ሲደሰቱም..... ሲናደዱም..... መሣቅ
ከተፈጥሮ ባህሪይ - መጠጋት ነው መራቅ?

## መኖሩ ከፋ እንጂ (1975 - ውበትና ልግመት)

ከያንዳንዷ ሰኮንድ.....
        እስትንፋስ ጀምሮ
የየዕለት ደቂቃ.....
        ሰዓት ተዘርዝሮ
የቀን የሌት ግዳጅ......
        ስሌት ተዘርዝሮ
የወራት ኮርቻ......
        በዓመት ተደምሮ
የፍጥረት ዘር ሕይወት.....
        ከተገኘ ምድር
ዘመን አልፎ ዘመን
        በተተካ ቁጥር
የታሪክ ምሰሶ.....
        ወጋግራ ሲዋቀር
ትውልድ አልፎ ትውልድ......
        በዘር ሲመነዘር
እጹብ ድንቅ ሲባል......
        የብቅለትሽ ዛባ
አንዴም ሳያለልስ......

አንዴም ሲታባ
ታሪክሽ ለታሪክ.....
ከታሪክ ሲጣባ
ፍም...... ነበልባል ገጽሽ.....
የልብሽ ስር አስኳል
የተፈጥሮሽ መዓዛ.....
የውበትሽ ጸዳል
ወደር እንደሌለው
አቻ የሚሆን አምሳል
ሺ - ሚሊዮን ጊዜ......
ተነግሮ ተጽፏል
እልፍ አዕላፍ ጊዜ.....
ውበትሽ ተስሏል።
አንቺ ግን ባመቱ..... በዘመናት ዕድሜ
ሁሌ ሙሽራ ነሽ...... የውበት ስያሜ።
የፍቅር ሰው ቋንቋ..... የፍቅር ሰው ስነቁ
አዲስ ስሜት ጠንሳሽ..... የልብ ስር ዕንቁ
ዕፁብ ድንቅዬ ነሽ....... የሰው ሁሉ ብርቅ!!
በውስጣዊ ስሜት.....
በደስታ ሲቃ
በትውልድ አንደበት

በታሪክ ሰው ቋንቋ
በከያኔው ብርዕ......
በሰዓሊው ቀለም
በቀራጩ ስሜት......
በጥበብ ሰው ዓለም
በትንሽ ትልቁ......
በአረጋዊው ሕይወት
በቅን በጠማማው በሁሉም አንደበት
ሺ - ሚሊዮን ቀና
እልፍ አዕላፍ ጊዜ.....
ሌሊትና መዓልት
እጹብ ውብ ተረንሽ......
ግሩም ድንቅ መዓዛ
ተነግሯል በአያሌው.....
ተጽፏል ሲበዛ።
አንቺ በየዓመቱ በዘመናት ዕድሜ
ሁሌ ሙሽራ ነሽ...... የውበት ስያሜ
የፍቅር ሰው ቋንቋ..... የፍቅር ሰው ስንቁ
አዲስ ስሜት ጠንሳሽ...... የልብ ስር ዕንቁ
እጹብ ድንቅዩ ነሽ...... የሰው ሁሉ ብርቅ!!

*****

የፍቅር ኩታ ጥበብ......
    መላበሻ ካባ
ከዕፅዋትም - ዕፅ ነሽ
    የአበቦች አበባ
የጠራራ መብረቅ.....
    የጨለማ ፀሐይ
የምድር ዙሪያ ውበት......
    የውስጥ ሕይወት ሰማይ
የንጋት ውጋጋን.....
    የስሜት እንግዳ
የተፈጥሮ ምስል.....
    የታሪክ ማለዳ
ዕፀተ - ተፈጥሮ...... የልብ ላይ ማርዳ
አንቺ ነሽ...... በአያሌው ውቢት ጽጌረዳ
    ዕፀ - ጽጌ - ረዳ!!

*****

የሚገኝ ቢሆን.......
    ልደት እንደገና
የዳግም ምስሌ.....
    አንቺን በሆነና
የዘላለም ዕድሜ......

ፍቅር በታደልኩኝ
የወዳጅ የጠላት.....
ስሜት በማረኩኝ
አሁንም አሁንም ሁሌ ጽጌ - ረዳ!....
ምነው በተባልኩኝ?
የአንቺ ጉህ ሲቀደድ.....
መድፍሽ ሲፈነዳ
የፍጥረት ዘር ስሜት....
ወደ አንቺ ሲነዳ
ሾተልሽን ረግሞ.....
ስምሽን ከመመኘት
በውብ ጸደል ግርማሽ
ቅኝት ከመቃኘት
ማነው ተፈጥሮሽን.....
በጥልቀት የናኘ
ሚስጥረ - ውበትሽን
ውልሽን ያገኘ?
ከልደት ባሻገር.....
ከለጋው ጥንቅሹ
ከማሚት ትንሿ.....
ከማሙሽ ትንሹ

ከኰልታፋው እሸት.....

ከድክ - ድክ ዕድሜ

ከጣፋጩ ልሳን.....

ከነማሙሽ ማሜ

እስከ ጐመዘዘው....

ኤጭ! አሁንስ ወዲያ!

እስከ ተባለበት....

የዕድሜ ክምር ጣሪያ

የጐህ ፍንዳታሽን.....

ጠረንሽን ሲያርቁ

ድንቅ እያሉ ብቻ.....

ውበትሽን ሲያደንቁ

ቁጥራቸው ስንት ነው....

ተወልደው ያለቁ?

*****

ቢሻሽ ተጠግተሽ.....

ቢሻሽ ብትርቂ

ፈልቀቅ ሲል ግትር....

ጨርሰሽ ስትሰቂ

ከፐላኔት ክፋይ.......

አካል ሰንጣቂ

ከማለዳው ጮራ......
        ከጉህ ፍንጣቂ
አስደጋጭ ውበትሽ.....
        ድርክክ ያለው ፀዳል
ከማንም ከምንም......
        ከሁሉም ይበልጣል
ዳኑግን፡-
        አልፎ አልፎ..... አልፎ አልፎ አንዳንድ..... ጊዜ
        አልፎ ለደስታ.... አልፎ ለትዝታ..... አልፎ በትካዜ
በአንዳንድ...... ጥረት ጠል
ለራስ ብቻ ባሉ..... ወስልቶ....... ዘርፎ - በል
ባልነበረ ስሜት....... ባልነበረ ዕውነታ
ባልገበረ መዳፍ.....
        ባልቃኘ ዕይታ
መልካም ብቅለትሽን......
        .......የውበትሽን ፀዳል
ከቶም ከፊት ሆነው......
        ......ቀድመው ይሻሙታል
በዚያም...... በዚህ..... ሾልኮው.....
        .....«ቅንጥፍ» ያደርጉታል
ያልዘሩትን አጭደው ለዛሽን አድርቀው

«መውደድ» ነው ይሉታል......

*****

መከራሽን መክሮ..... ስታስቢ ያስብሽ
አፈር..... ያለበስሽ
ለጥ ውሃሽ.... ውሃ..... ደርሶ ያቀበለሽ
ደፋ ቀና ያለ..... ተግባር የለገሰሽ
«መከራ - በላይ» ሳይሆን...... እንደራስ ያቀፈሽ
ከጉርፍ..... ያካለለሽ
ከእኩይ..... የደበቀሽ
ጭጋግ አረምሽን..... ሰንኮፍ የነቀለ
ዕፀ - ችግኝሽን..... ዘርሽን የተከለ
እርሱ ላንቺ ሳለ.....
የድርሻውን ድርሻ...... ላመል ሳይወጣ
ለክፉ ቀን ውሎሽ..... ላዘንሽ ሳይመጣ
ያርጥብሽ...... ያድርቅሽ
አንድ ቀን..... ሳይልሽ
መኸርሽን.... ጠብቆ
ውበትሽን..... አድንቆ
«መኖሩ ክፉ እንጂ»...... በመውደድ ያሞኘሽ
በሽፍንፍን ሽፋን..... በሽፍጥ የቀጠፈሽ።

## ሺ - ጊዜ ቢሞቱ (1975 - ዐላማ)

የሰው ልጅነት ኑሮ...... የሕይወት ቆይታ
የመኖር ጉጉቱ..... የምኞት ሕቅታ
ሐዘን ሆነ ችግር..... ተድላና ደስታ
የዕድሜ ክምር ጣሪያ...... የዕድሜ ጣዕም ሲሳይ
ከተፈጥሮ ደንቦች...... ከሕጐች መስመር ላይ
ከአንድ ዓመት..... ከአንድ ዕለት...... ከደቂቃ በላይ
ከማከተሚያው ሰከንድ...... ተዛንፎ ላይታይ
ከሰዎች መካከል..... በአንዳንዶች ሕሊና
ከቶ ለምን ይሆን?....... ተንኮል ያጣላበት..... የጥፋት ደማና
እኮ ለምን ይሆን ከሐቅ የሚሸሹ
ለወራዳ ተግባር ምንጣፍ ሆኖ መኖር...... አጥብቀው የሚሹ
ሸፍጥ የገየደውን....... ወልጋዳ ማቃናት
የሃኬተኞችን ድውይ...... ጽልመትን መግራት
ለሐቅ ድል ትግል...... በዓላማ ላይ መጽናት
ከዕብሪተኞች መዥገር....... በደም ውሃ መጽዳት
በትግል ላይ ውደቆ....... ለታሪክ ድል መብቃት
ለተከበረ ሞት..... ለተከበረ ስም
ሃሌታው «ሀ» መሆን....... የአኩሪ ታሪክ መቅድም
ከቶ ለምን....... ይህ መልካም ቅን ሥራ

ጦር..... ጐራዴ..... ሆኖ...... እሳተ ገሞራ
የሚያሳድዳቸው....... ከዚህ ዕውነት ጐራ
ለምን ይሆን ከቶ...... ይህን የሚፈሩ
በኋልዮች መንገድ...... ሲጓተቱ የሚያድሩ?
ለሰው ልጆች ሕይወት..... እውነተኛ ፍቅር
ግንባር ቀደም ሆኖ...... መፋለም መጋተር
ይህም ቆራጥነት..... ይሄም ወኔ ይቅር
እሺ - ምናለበት.....
በራስ ላብ ጠብታ...... በራስ ድካም መንገድ
ቀናውን ጐዳና...... ለሰው ልጅ በሚቀድ
ከራስ ሕይወት ማዶ...... ለመላው አካል ሰው
አካል ጌጡን ሰጥቶ...... ደሙን በሚያፈሰው
የሚደረግ ደባ...... የሚሸረብ ተንኮል
ምናለበት ቢቀር....... በሐቅ ቢከለል?
ከሻገተ ጠባይ....... ከጠነባ ቅርፊት
ከራስ ሕይወት ትግል...... ከራስ ሕይወት ሙግት
ከጠማማ ባሕርይ...... ከራስ ዕምነት ፈሊጥ
ከሕሊና ቅቅት...... ከራስ ሽሽግ ወሲጥ
መላቀቅ...... መዳቀቅ...... መፏተግ ቢደረግ
ምናለ ቆሻሻው...... ዕድፉ ቢጠረግ?
እሺ ሁሉም ይቅር...... እንበል ሁሉም ይደር

ከወረዛ ሕይወት....... ሐቅ እንደራደር
ግን.......
ዳግም ላለመንቃት...... ከማንቀላፋቱ
ከብጣቂ ሱቲ...... ከእስር ግንዛቱ
ከሶስት ሜትር ጉድጓድ..... «ከግባ - መሬቱ»
የሚያስቀር ዳኛ...... ገላጋይ ለማይኖር
ዳግም ተመለሶ...... ሰው ሆኖ ላይኖር
ለምን ይሆን ከቶ...... ሐቅ የሚሰንጉ
ለብስባሽ ሥርዓት....... ማገር ጭቃ ሆነው....... መኖር የሚጓጉ?
ጊዜ የሚያወጣውን....... ራስን ቢደብቁ.....
እልፍ ኩንታል ውሸት...... ሃሰት ቢሰልቁ
አንዲት ማንኪያ ዕውነት...... ላይወጣው ከሐቁ
ምናለበት ሰዎች...... ለመልካሙ ተግባር..... በሃሳብ ቢጨነቁ
ዳቦ ቆሎ ትተው...... «ሕይወት» ቢሰንቁ?
ሐቃቸውን ይዘው....... ለሐቅ ቢሰለፉ
ለጋራ ድል ሕይወት...... ታግለው ቢሰየፉ
ለነፃነት ሲሉ....... ለሰላም ድል ቢያልፉ
አሁን ምናለበት?........ ሥጋ....... ሽንኩርት...... ሆነው ታርደው ቢከተፉ
ስጋም ያው ስጋ ነው..... ፈራርሶ የሚከትም
ምንጊዜም የማይቀር..... የአፈር ዕዳ ሸክም
ይልቅ ሕያው ነገር........ ቋሚ ሕይወት ተክተው

ምናለ ቢኖቱ! ከመቃብር በላይ...... የሚውል ስም ትተው?
ሐሩር ረሞጫውን....... ዳገት ቁልቁለቱን
መራራውን ትግል....... እሳት አንፋሎቱን
እንደ ጀግናው ቆስለው እንደ ጀግናው ወድቀው
በሕይወት ሕቅታ...... እበም ፍሳሽ ዋኘተው
በሚያልፍ ሕይወት አፈር - ወርቅ አንቄ ተክተው
ምን ጊዜም የማይሞት...... ሕያው ታሪክ ሰርተው
ምናለ በክብር...... ከአፈር ቢከተቱ
ከአንዴም....... ሁለት ሶስቴ...... ሺ - ጊዜ ቢሞቱ?

............

............................

................................................

# በጾታዬ አትፈትነኝ (1976 - እኩልነት)

የመከራ ጽልመት ግርዶሽ

የዘመናት ሮሮ ሲቃ

የመደብ አካል ትምክህት......

የበደል ብሶት ጩኸት ሰቆቃ

አሁንስ በቃኝ...... ይብቃ!

«በቃኝ» አልኩ....... የግፈኞች መዳፍ ጫና

ምነው ጃል!.....

በነፃነት አገር ባርነት በብርሃን አገር ጨለማ

ፀአዳ ሕይወቴ የሚገማ

ጤና...... ሕሊናዬ...... የሚደማ?

ምነው በል!......

ለጥ...... ባለ አገር ምድር...... ዝባዝንኬው አፋፍ ገደል

በእናትነት ሕይወት ጣጣ....... በሴትነት ድርብ በደል?

እኮ! ለምን?

የከረረ እልህ መቀስ..... የወሳኝ ዓላማ አርኪ ድል

የሩቅ ጉዞ በትረ - ነፃነት...... ፈውሰ - ሕሊና አኩሪ ገድል

ትግል!...... ትግል!...... ትግል ነው ትግል

«መስዋዕትነት» ነው...... የልብ ምኞት ፍሬ ሰብል።

የማጀት ድብቅ ገበናዬ
የስም ብቻ ስብዕናዬ
የጭቆና ንፍረት ሕልውናዬ
የጉስቁልና ሕይወት ገላዬ
ይገለጥ ይውጣ በአደባባይ
ወንድም ከአንተ ጋር ይተያይ
ወንድም ከአንተ ጋር ይወያይ
ውሌ ከውልህ ይናኝ
ትግሌ ከትግልህ ይናኝ
ዓላማዬ ከዓላማህ...... ዓላማህ ከዓላማዬ ይቆራኝ
ግቤ ግብህ ነውና!...... ድልህ ድሌ ነውና
    የትግል ጕራህ ለድል ይጥራኝ!!
ይጥራኝ....... ይጥራኝ....... ይጥራኝ!!
    ብዬ...... ከተሰለፍኩ
    ሞትክን በሞቴ...... ሞቴን በሞትህ ለወጥኩ
    ወንድም ብዙ ዓመታት አሳለፍኩ!
«የጽለመት መከራ ማርከሻ
የጾታ ትምክህት መንቀሻ
የነፃነት ውል ማሰሪያ
የእኩልነት መብት ማብሰሪያ
የአንድነት ቋሚ መልህቅ...... ዘላቂ ሰላም የሚሰፍነው

የተጨቋኝ መደብ ብሩህ ተስፋ..... መራራ «ትግል» ብቻ ነው።

ለሚል ሃቅ ዕውነታ

እወንት እንጂ የእኔ ዕውነታ

ትግል እንጂ የእኔ ገጽታ

የግማሽ ሕይወቴን ግማሽ ኑሮ.....

ድርብ በደሌን የሚፈታ

የትምክህተኞችን..... ትምክህት..... የሚገታ

የዕብሪተኞችን...... ዕብሪት....... የሚረታ

«መስዋዕትነት» እንጂ ምን ሊኖር?....... ለእኔ ሕይወት ሌላ እውነታ?

የዓላማህ ውል ቅንጅት..... የብሩህ ዘመን ግኝት ፋና?

የችግርህ....... ተቻጋሪ...... የመከራህ ተጋሪ...... የትግል ክንድህ

እንዳሰብኩህ አንተም አስበኝ

እንዳመንኩህ አንተም እመነኝ

«ወንድም» ስልህ «እህት» በለኝ

ለሩቅ ዓላማ ግብ እልመኝ

ለጋራ ትግል...... ለጋራ ድል ሕይወት...... ተመኝኚ

ለብሩህ ዘመን ተስፋ..... ለሰው ልጆች ሰላም ትግል...... ቅበረኝ

«በዓላማዬ»...... «በተግባሬ»..... እንጂ ወንድም በጾታዬ አትፈትነኝ

በጾታዬ...... ዓቅልለኝ!

ለስሜትህ...... አትመኘኝ

ለፍትወትህ..... አታቅልመኝ!

እና፡-

ወንድም! «ወንድም» ስልህ እህት በለኝ

በዓላማዬ...... በተግባሬ እንጂ...... «በጾታዬ» አትፈትነኝ!

ለስሜትህ...... አትመኘኝ

ለፍትወትህ..... አታቅልመኝ!

እናስ...... ደሞ

ደምህ በደሜ ቀልሞ

ሕልውናህ በሕልውናዬ ታምኖ

ፅንስህ በአንጀቴ ሰፍኖ

«ውልደትህ» በጭንቀቴ.... «ዕድገትህ» በደም ጡቴ ገኖ

ኑሮዬ ለመኖርህ ካክኖ

ክብሬ ለክብርህ ሰክኖ

ሳይበላ ላበላ..... ላይጠጣ ለጠጣ...... የአንጀት ፍቅር

ምላሹ እንዲህ ነበር?

በሴትነት ጾታ መከፋት.... መገፋት ነበር እውን ዕጣው?

ለእናትነት ሕይወት ዕድል..... ለሴትነት ክብር ድርሻው?

የሰውነት ክብሬን አጥቼ

ብሶት ስቃይህን ተጋርቼ

መከራህን በመከራዬ ገፍቼ

ሕልውናዬን ለአንተ ሰውቼ

ኑሮ ሆኖ ኑሮ በኖርኩ
ያለ በደሌ በተበደልኩ
የጧት ታሪኬን በተነፈኩ
እስቲ ምን አጠፋሁ ምን በደልኩ?
ለማሳዘን ሳይሆን ለማፀፀት
እስቲ ልጠይቅ አንድ ዕውነት
«ሃገሩን በደሙ ለአስከበረ..... ጀግና ለአፈራ እናት እንጀት
ጠቢብ - ጠቢባን ላመነጨ..... ለዳግም ውልደት ዳግም ፅንሰት
ለስንትና ስንት ፈላስፋ...... ለታላቅ ታሪክ ማህፀን ዕብርት
መቼ መከፋት?...... መቼ መገፋት?...... ነበር ዕጣው
የእናትነት...... የሴትነት..... ጾታ ታሪክ ድርሻው?
ለቃልህ ቃል እምነቱ
ዓላማህ..... ነውና እውነቱ
ተናገር!...... ይገባኝ ነበር መበደል
ሕልውናዬ ጨልሞ..... ሐቁ በሸፍጠኞች መገደል?
ወንድም.....
ይቅር ግድ የለም
ይቅር በይኝ እንድትለኝ...... ከቶ ወንድም አልፈልግም
የእኔና የአንተ የአንጀት ፀፀት..... የልብ ልብ መሪር ሃዘን
ቂምን በቂም...... በደልን በበደል..... መቁጠር ሳይሆን
ዓላማዬ ከአንተ ዓላማ...... የድል ግቡ አንድ የሚሆን

«በትግል» ነው! የእኩልነት ነፃነቴ...... ውል አግኝቶ የሚሰፍን እና! ወንድም......

የዓላማህ ውል ቅንጅት...... የብሩህ ዘመን ግኝት ፋና
የችግር ተቻጋሪ..... የመከራህ ተናጋሪ..... የትግል ክንድህ ነኝና
እንደአሰብኩህ አንተም አሰበኝ
እንዳመንኩህ አንተም እመነኝ
«ወንድም» ስልህ «እህት» በለኝ
«ጓድ» ስልህ «ጓድ» በለኝ
ለሩቅ ዓላማ ግብ አልመኝ
ለጋራ ትግል...... ለጋራ ድል ሕይወት..... ተመኘኝ
እንጂ ወንድም..... «በጾታዬ» አትፈትነኝ!!
ለስሜትህ አትመኘኝ
ለፍትወትህ አታቅልመኝ

..........

..........................

...............................................

..................................................................

## ትዝታ (1977 - ትላንት)

የዕልፍ አዕላፍ ዕልፈተ - ቀን
የሩቅ ዕድሜ የሩቅ ዘመን
የኑሮ ትግል ሂደት ትውስታ
የዕውነታው «እውነት» ዕውነታ
        የትላንት ሕይወት አካል እሙን
        የደግ የክፉ ነገር ክንውን
        በሩቅ ምናብ በአሁን ቅኝት
        በሰመመን አመጽ ፍጭት
በዛሬ ዕድሜ ሲዳሰስ
ደስታው በሲቃ ሲታመስ
ሃዘኑ በሃዘን ሲታወስ
ጓድ ገበናው ሲታሰስ
        ያለፈ ሕይወት ሚስጢር ኑሮ
        በፉጨት - እንጉርጉሮ
        በጥላቻን - በሰቀቀን
        በፍቅር - በሰመመን
        በትዝብት መነጽር ዕይታ.....
                በዓይነ ሕሊና ሲፈተሽ
        ትውስታው «ትውስ» ሲል.....

ሕይወት ወዲያ ወዲህ ሲሸሽ
ትዝታ!...... ትዝታ!..... ነው መደብሩ
ትዝታ!....... ትዝታ!....... ነው መደብሩ
ትዝታ!....... ትዝታ!....... መደበቂያው
በድን አካል ሙት አምሳሉ
ቀሪ ሰነድ - ቋሚ ቃሉ።
ትዝታ፡-
የአባት የእናት የጓደኛ
የቤተ - ሰብ የፍቅረኛ
የጫጉላው ቤት ፍንድቅ ድቁ
የጦር ሜዳው ትንቅንቁ
የጀግንነት - ሕይወት - ስንቁ
የልጅነት ለጋ ቋንቋ.....
ጣፋጭ ልሳን ጣመ ዜማ
የአፍላ ጉልበት - ፍርጥም ግርማ
የነበረው፤ እንዳልነበር
ትላንት ዛሬ ሳይሆን ሲቀር
የሩቅ አካል የሩቅ ሕይወት
ከአሁን ዕድሜ ከአሁኑ ስሜት
ፍጭት ይዞ የሃሳብ ቅኝት
ሲያብጠለጥል - ሲያነታርክ

ሲያብሰለስል - አንጀት ሲያኝክ\
ሂሳብ ወዲህ ሃሣብ ወዲያ
ተወጥኖ ተወጥሮ
ሰው እያየ ሰው የማያይ
ትላልቅ ዓይን አሣውሮ
ዛሬም ነገር ነገም ዛሬ
ሁሌም እንጭጭ ሁሌም ፍሬ
ሁሌም ብስል ሁሌም ጥሬ
ትኩስ ሆኖ ሃሣብ ሲያምጽ
አፈር ምሶ - ሙት አላውሶ.....
ብትን አካል ንዶ ሲያንጽ
«ትላንትና» ሲበረበር - በደቂቃ ዘመን ሲያመሽ
በዓይነ - ሕሊና ሲፈተሽ
ትውስታው «ትውስ» ሲል
ሕይወት ወዲያ ወዲህ ሲሸሽ
ትዝታ!...... ትዝታ!..... ነው መደብሩ
ትዝታ!...... ትዝታ!...... ነው ምስክሩ
ትዝታ!....... ትዝታ!...... ነው መደበቂያው....
በድን አካል ሙት አምሣሉ
ቀሪ ሰነድ፤ ቋሚ ቃሉ።

# የውል ስም ሆነና (1968 - ልዩነት)

የአቋም - በገጽታው
በሳቅ - በፈገግታው
በሀዘን - በደስታው
በደመ - ሕይወቱ
በአጥንት - ስሌቱ
በዕይታ - ሲከፈል
በአካል - ሲደለደል
በስብዕና ስብ - በጥንስስ አስኳሉ
በሰው ሰውነት ሕግ በአምልኮተ - አምሳሉ
ሰው በሰውነቱ በእርግጥ ሰው ይባላል
የወል ስም ሆነና ሁሉም በአንድ ይጠራል።
ግና...... ሲተነተን
በተግባር....... ሲፈተን
መለኪያው..... ሲመጣ
ሚዛን ላይ ሲወጣ
እንዲያው..... እንዲያ ሆኖ
ያለእምነቱ....... ታምኖ
እንዳልታየ..... ታይቶ

በይለፍ..... ተትቶ
ታውቆ..... እንዳልታወቀ
ከአደባባይ ቆሞ...... እንደ ተደበቀ
ማህጸኑ..... ሳይቃኝ
ውስጠ ውስጡ ሳይገናኝ
እንዲያው በደፈና በቀለለው መስፈርት
በጐላው..... በጐላው..... በጉብታው ቅጥፈት
የቀን ውሎ መልኩ
የሴት አዳር ልኩ
የቁም - ነገር መልኩ
በተግባር...... ክፍልፋይ
ውስጠ - ውስጡ..... ሲታይ
ንፁህ ልብ አደፍራሽ
በመርዝ ዕድፍ ለዋሽ
የሽፍጥ ክምር...... ጉዝጓዝ
ሆደ....... ልብድ መጋዝ
የታሪክ አዳፋ...... የአጉል ጠባይ ብካይ
ሲቀርቡት የሚርቅ..... ሲያምኑት የ'ሚከዳ ስንት «ሰው» በዓለም ላይ?
ከራስ መደብ - ስሌት
ከራስ ከርስ - ሙሌት
ከግለኝነት - ሕልም

ከራስ ኑሮ - ጥቅም
ራስን - ከማሸቀርብ
ለንዋይ - ከማቅረብ
ከዚህ ሌላ ዕውነት
ከዚህ ሌላ እምነት
ከራስ በቀር ሕይወት
ቢጠፉ...... ቢከስም
የተፈጥሮ ሕይወት ውበቷ ቢያከትም
ጨረቃ ባትወጣ..... ፀሐይ ብትጨልም
አእዋፋት...... ቢያበቁ
ምንጮች....... ባይፈልቁ
ደኖችም...... ቢደርቁ
የሀገር ፀጋ ቢነጥፍ
የሀገር ሕይወት ቢረግፍ
ምንም ይሁን ምንም
ሽቅብ ይሁን አግድም
ካልሆነ በስተቀር የግሉ ፍንደቃ
የዚች ምድር ነገር ጨርሶ ቢያበቃ
ዕድገት ወይም ውድቀት
ሰላም ወይ ጦርነት
ጥራት ወይም እንከን

ለእርሱ ምኑ የማይሆን

ነዋየ - ኑፋቄ..... እርኩም ክብረ - በላ

የሕሊና ቅንቅን..... እሾክ - አሜኬላ

ቢያጥቡት የማይጠራ...... ቢያሰጡት የማይደርቅ

የመልካም ነገር ጠንቅ

በማር የራስ መርዝ - እኩይ ነፍሰ ገዳይ

ሲቀርቡት የሚርቅ...... ሲያምኑት የሚከዳ ስንት «ሰው» በዓለም ላይ?

ግን የወል ሆነና

ሰው «ሰው» ተባለና

ይህም «ሰው» ይባላል

በድምር - በድምር - በጥልቅ ይጠራል።

ሆኖም በወል ውሉ

ከጋራ ስም ቃሉ

ካልሆነ በስተቀር የሰው ምስል ምስሉ

ከምድር...... ከሰማዩ..... ከአጽናፍም ይርቃል

በቁም ነገር መድረክ ሰው ከሰው ይለያል።

«የታሪክን ማዕዘን ማዋቀሪያ ሥሩ

የማንነትን ምን ማያ መነጽሩ

የሰው ሰውነት ምስል ዳር ድንበር ወሰኑ

የውስጠ ባሕሪ ሀቅ ዕውነት ልሳኑ

የቅን ውሎ መድረክ ተግባር ነው ሚዛኑ።

ብቻ ምን ያደርጋል.....
በስብዕና - ስብ በጥንስስ - አስኳሉ
በሰው ሰውነት - ሕግ በአምልኮተ - አምሳሉ
ሰው በሰውነቱ በእርግጥ ሰው ይባላል
የወል ስም ሆነና ሁሉም በአንድ ይጠራል።»

## ቼቼ - ሰንጋው መዘዜ (1973 - ሃሳብ)

የሳቅ - የትካዜ
የቅርብ - የሩቅ ጊዜ
የመንፈስ - ምርኩዜ
ቼ! ጐራው - ጐበዜ
ቼ! መገን - ቼ! መገን..... ቼ! ሰንጋው - መዘዜ
ቼ! ፈረሴ ቡሎ
ይጠብቅህ የለ...... የሩቅ መንገድ ውሎ?
ታዲያ ምን ሆንክብህኝ?
ምነው ፈዘዝክብኝ?
ቼ! ስልህ ቼ! በለኝ
ልጋልብህ ወይ ጋልበኝ
ቼ! ፈረሴ ጥሪኝ

የሜዳው የቋጥኝ።

ቀልቤ ካልፈቀደው.....

ካላሰኘው ወስደህ.....

አታፍዘኝ...... ፈዘህ

እኮ! በል ብርርር..... በል

......ግመስ ተራራውን

ሰንጥቅ - ደመናውን

በተርመሰመሰው

ዝም እርጭ ባለው

በቁልል ደመና በተበታተነው

በቅን - በጠማሞች - በዕብሪተኞች ሰፍር

በሕዝባዊ ጀግኖች በድል ሰንደቅ መንደር

በቀጥተኛው መስክ በአንድ ዕውነታ መስመር

ቼ! ሰንጋው መዘዜ...... ጃቱን ቀድመህ ብረር

በታሪክ ጐዳና.....

.......በሀቅ አውራ መንገድ

እንዳሻህ ሁንልኝ

......እንዳሻኝ ልራመድ

የሩቅ ሰው ናፍቆቴን.....

......ምኞቴን ልወጣ

ያልሆንኩትን ልሁን......

ያማረኝን ላምጣ።
ቼ ፈርሴ ገሩ
ገበና...... ሚስጢሩ
ምድሩ ወይ ጠፈሩ
ሁሉ ላንተ አገሩ
ሁሉ ቤት ሰፈሩ
ላንተ ምን ላይሆንህ......
ላታገኝ እኩያ
ምን ውሎ አሳደረህ.....
ፈረሴ አባ ብያ?
ቼ! ሰንጋው ፈረሴ
የሕሊና - ጉርሴ
ቶሎ ቶሎ ድረስ ና! ስልህ ፈረሴ።
ከጐኔ ሰው ጠፍቶ.....
ስቆ አነጋጋሪ
የልብ ወዳጅ ሳይኖር.....
ጭንቀቴን ተጋሪ
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ.....
ከፍቶኝ ተጨብጨ
«አልቦ» መዳፍ ሆኜ......
በጽልመት ተውጨ

መላ ውሉ ጠፍቶኝ
የቀለለው ከብዶኝ
ውዬ ሳድር ከፍቶኝ
የመንፈስ ምርኩዜ
ቼ! ሰንጋው መዘዜ
አንተ ስትደርስልኝ.....
        በቅጽበት ስትመጣ
ፈጥነህ ስትቀርብልኝ.....
        በአንተ ላይ ስወጣ
ያን ጊዜ ነው ለኔ.....
        ሌሊቱ የሚነጋ
ፀሐይ ቤቴ ዘለቃ.....
        የሚከበኝ ፀጋ።
ያን ጊዜ ነው ለኔ.....
        ጽልመት የሚርቀኝ
የተከፋው ስቆ......
        ፈንድቆ የሚቀርበኝ
ያንጊዜ ነው ለኔ.....
        ተዝቆ የሚታፈስ
ወርቅ...... አልማዝ..... የሚታፈስ
ዓለም ትንሽ ሆና.....

ከሰፌድ የምታንስ፡፡
ተራራው ተንዶ......
ከሜዳ የሚሰፋ
ትንፋሼ ኮረብታ......
ቋጥኝ የሚገፋ
ላንቃዬ ነበልባል.....
......ዕሳት የሚተፋ
ግንባሬ እልፍ እልፉነ.....
......እልፉን የሚደፋ፡፡
ያንጊዜ ነው ለኔ.....
.....ሁሉ ለኔ ትንሽ
እንኳን ትንፋሽ ወጥቶኝ.....
......ሳየው የሚተርሽ፡፡
ቼ! ፈረሴ - ትዕግሥት
የነገዬ...... ሕብስት
በልብ እሳት ሞገድ
በጭንቀት ቀን መንገድ
በቁጭት ትዝታ
በትዝብት ውልታ
በሕሊና ፀፀት
በታፈነ አንደበት

በደም በታጠበው
በአጥንት በታጠረው
በደም ሰንበት...... ጐራ
ውሰደኝ ባር ማዶ......
......ልየው ያንን ስፍራ
ሰንጋው...... ትዝታዬ
የቀን የማታዬ
ቼ! ስልህ..... ቼ! በለኝ
ልጋልብህ..... ወይ...... ጋልበኝ
ከለጋው እንጭጩ.....
.....እሰይ ሎጋው ሸቦ
ከእግሮቼ..... እግር አልቦ
ከቀጋው ከአጋሙ.....
..... ከዋርካው ሥር አድባር
ከእጆቼ..... የብር - አምባር
አንገቴን..... መጣብር
ከዕትብቴ...... መቃብር
ከሰንበሌጥ...... ልባስ.....
ቅርስ - ወዘናዬ
ከፍ ከፋት..... ቪላዬ
ከአደባባይ መውጫ.....

......ከከት - አጉዛዬ
ማጌጫ...... ካባዬ
ከአሹቅ..... ከጠሮሾ......
......ጉመን ምሳ ራቴ
ከጮማ - ብስኩቴ
ከአፈር ቁልል አልጋ
ከድርቆሽ ፍራሽዬ
ከአረግራጊው መደብ.....
.....ከሌጦ አንሶላዬ
ላንድ አፍታ ልገናኝ
ዓይነ ሕሊናዬ.....
......ያንን ሕይወት ይቃኝ
እና! በል ፈረሴ......
ውሰደኝ ሰፈሬ
ከዕትብቴ..... ከአፈሬ
ከትውልድ መንደሬ
በባዶ..... ፍንድቅድቅ
በዳዴ....... በንፉቅቅ
በድክ........ ድክ....... አቅሜ
በእንጭጭ...... እንቡጥ ዕድሜ
በኮልታፋ...... አንደበት

በምኞት...... አቀበት
ውርጄ....... ወጥቼ
ከጭቃው..... ጨቅይቼ
ፈንድቄ...... ጨምቼ
ስቄ..... ተከፍቼ
እበንክብል...... በእንብርክክ
ያደኩበትን....... መስክ
እንዴ - አጫውቼው
ፍቅሬን...... ገልጨለት
የልቤን....... ትቼለት
ተመልሼ....... ልምጣ
የናፍቆት ምስጢሬ.....
እሳት ሆኖ ይውጣ፡፡
ታዲያ...... እግረ - መንገዴን
እስካሁን..... ልማዴን
«የመስክ...... የመንደሬ
የወንዝ..... የድንበሬ
የዘር ማንዘሬ..... ደብር
የዕትብቴ..... መቃብር.....»
ተብሎ - ሲወሳ
ስሙ በወደቀ...... ስሙ በተነሳ

እንዲያ...... የሚያደርገኝ
የሚያንሰፈስፈኝ
አንዳች ነገር ደርሶ......
　　ውስጤን የሚያምሰኝ
ለምን እንደሆነ......
　　ጠይቄው ልመለስ
ፍቅሬ እንዳለ ሆኖ.....
　　መንገዴ ይቀነስ።
ወግ...... ባህል..... አላብሶ
ሥጋ...... ደም..... አጣቅሶ
የቀረበው ካለ......
　　ውስጥ አንጀቴን ምሶ
ከእንግዲህ ያውጣልኝ.....
　　ይውሰደው መልሶ።
እምነቴን...... ማቅለሙ
　　ምናቤን...... ማከሰሙ
　　መንፈሴን መበተን.....
　　　　ቀልቤን መስረቅ ይተው
　　ሁሉ ሃገሬ ሆኖ።
　　　　መኖሬን ይወቀው።
　　እኮ...... በል ፈረሴ.....

....... እሰይ የኔ - ሺጋ

እሰይ...... የኔ ሎጋ
ቼ! ሰንጋው ፈረሴ
የነፃነት....... ጉግሴ
የሩቅ ድግስ..... ጽንሴ
የመንፈሴ..... ልባስ
የድካሜ...... ትራስ
የምኞቴ....... ወደብ
የስሜቴ....... ወገብ
የአበባ...... ንጣፌ
የሕሊና....... ጧፌ
አንተ - ባትኖርልኝ
አንተ - ባትደርስልኝ
ወጊድ! ስል ባትነጉድ......
ና! ስል ባትመጣልኝ
ይህን...... ድህነቴን
ይህን..... ጌትነቴን
ግዙፍ...... ፍላጎቴን
ምስኪን...... ሰውነቴን
ዝብርቅርቅ...... ቅብጥብጥ.....
ዳር የለሽ ስሜቴን

በጫንቃዬ...... ይገፍ
በአንጀቴ...... ጐዝጉዝፍ
ስንት ጉድ...... አርግዤ
መለስ ቀለስ ስል......
......ገብቼ ስወጣ
ላስቀምጥ ስነሳ......
ወስጄ ሳመጣ
የደጅ የቤት ጉዴን.....
በጉድ ሳበለጥል
ይሄኛውን ሳወርድ.....
ያንን ሳንጠለጥል
ይሄኛውን ስስብ.....
ያኛውን ስገፋ
ጠቅልዬ ሳነጥፍ......
ቀድጄ ስሰፋ
የኔን ለርሱ ትቼ.....
እኔው በእርሱ ስስቅ
እርሱ የኔን ውሎ.....
እኔ የርሱን ስንቅ
ውሎዬ እንዲህ ሆኖ......
አይሆን ሆኜ ሳድር

በምን አቅሜ ችዬ......
እንዴት እሆን ነበር?
አንተ ባትኖርልኝ.....
ና! ስልህ ባትመጣ
ምኑን ከምን ይዤ......
ነበር ይም'ወጣ?
ቼ! ቼ!......ቼ! ፈረሴ አደይ
የውስጥ ሕይወት..... ፀደይ
ቼ! ፈረሴ...... ጉብል
የሕሊናዬ.....ብል
ቼ! ስልህ ቼ! በለኝ
ስጠራህ ወይ በለኝ
ሽምጥ ቼ! ጉበዜ
ቼ! ሰንጋው መዘዜ
ውሰደኝ...... ብር አምባር
ከባሕረ - ኖቱ...... ከጅረቱ ልግባ
ይሄ ሁሉ ቡንኝ.....
ይሄን ሁሉ ክምር
ይሄ ሁሉ ጥቅል.....
ይሄ ሁሉ ረብጣ
ይሄ ሁሉ ረብጣ.....

ይሄ ሁሉ ፓውንድ
እዚያ ተወዝፎ......
እሳት ከሚነድ
እንዲያ ጥንቡን ጥሎ.....
በምላስ ከሚላስ
በል ሰንጋው መዘዜ......
ዛቅ አድርጌው ልምጣ
ምንነቴን ትቼ.....
እኔነቴን ላውጣ።
እህል ጋሻ ስቁ
ሃቅ የሕይወት ስንቁ
መደፈር ኩዳዴው.....
......ድል የባህል ወጉ
ሞት...... የታሪክ..... ሥርጉ
የሀገር ሕይወት ሰንደቅ
እኔም እንደቋራው........
......«የመቅደላው» መብረቅ
አንተም እንደ...... «ታጠቅ»
እንደ እምዬ አደባሩ......
ኵስትሬ ኩይሳው
እንደ «አድዋው» ቀንጥስ.....

እኔም እንደ አርበኛው
አንተም እንደ...... «ዳኘው»
እንደ «አላጌው» ኮርማ.....
እኔም እንደዚያ ሰው
አንተም እንደ........ «ቃኘው»
እንደ አገር ዳር ወሰን.....
«የቀይ ባህር» ግርማ
እንደ ሰሜን ኮከብ
ያንን አገር ደም ግርማ
እኔም እንደዚያ ሰው......
እንደዚያ ሰው ሎጋ
አንተ እንደ..... «አባ - ነጋ»
እኔም እንደ ጃሎ......
እንደዚያ ሰው ውሎ
አንተም እንደ...... «ቡሎ»
በዕብሪት...... ከፈለሰው
ከተርመሰመሰው
ቼ! ሰንጋው መዘዜ......
በል «ታጠቅ» እንበለው
ገብተን - እናምሰው።
ጐራዴያችን ይዝለል.....

ከመሃል ከመሃል
ከአንገት ከአንገቱ ላይ......
ከደረቱ ይዋል።
ለጅግና - ሰው ወጉ
ሞቱም እንደ ሥርጉ
ሆ! ይባልለታል!
ይጨፈርለታል!
ሆ! ይባለልለታል.......
«ሆ»! ጉሮ - ወሸባ
ቀንጥሶ...... ቀንጥሶ......
አምሶ ሲገባ።
ዝለቅ - ቼ! ጎበዜ
ቼ!...... ሰንጋው - መዘዜ
ጐራው! ጃሎ ጐራው!.......
ይባላልን...... «መገን» ይደርደር «ቅኝቱ»
የአንተም የኔ ውሎ.......
......ይነገር ግኝቴ።
ቼ! ቼ!...... ቼ! የትላንት ትዝብቴ
ከዕድሜው ፀጋ..... ሳልርቅ
ለዛ ውበቴ..... ሳይደርቅ
ይሄን ትቼው ልለፍ......

ያን..... ነዶ - ላጥብቀው
ከገመገም ወዲህ ከገመገም ማዶ.....
ዳር መሃሉን ልየው......።
የተፈጥሮ ውበት......
ወርርቅ አምባር ጨፈቃ
የምድር የሰማዩን......
ብር አሉሎ ላንቃ
የፀሐይ ከዋክብቱን.....
የህዋው ጨረቃ
ደስታ መከሬን.....
......የዕልፈት ዘመን ሲቃ
ድር ማጉን ልቋጨው.....
......ጠማማውን ላርቅ
ተፈጥሮን ገርቼ.....
.....ተፈጥሮን ልሰንቅ።
እና በል ፈረሴ......
ቼ! ጐራው ጐበዜ
ቼ! መገን ቼ! መገን......
ቼ! ሰንጋው መዘዜ
በታሪክ ጐዳና
በሐቅ አውራ መንገድ

እንዲሻህ ሁንልኝ......
እንዳሻኝ ልራመድ!!

# የሞተማ - ሞተ (1965 - ቁጭት)

የሰው ሰውነት መብት..... ነፃነት....
......በሰው ሰውነት ሽፍጥ ቢገፋ
የሰው ሰውነት ሰብዓዊነት.....
......በሰው ሰውነት ዕብሪት ቢጠፋ
ለመኖር...... አዎ! ለመኖር......
ሰው ለመሆን....... ሰው ለመባል..... ምኞት ተስፋ
ወጣ!........ ወረደ!....... ባከነ!...... ማሰነ!......
ሰው ለመሆን..... ሰው ለመባል..... ምኞት ተስፋ።
ግን ምን ያደርጋል?......
አልሆን አለ...... ምኞት ከዕውነት ተገፋፋ.......
እልህ ከአቅም...... ሕይወት ከዕድል ተፋጠጠ
እንደወጣ....... እንደወረደ......
እንደማሰነ...... እንደባከነ..... እንደለፋ\
ሳያልፍለት...... ተደፋ።
ቀረ...... አዎ...... ቀረ

አቅመ - ጉልበቴ ተሰበረ
ተስፋው ጨለመ....... ሰው የመሆን ዕድሉ.....
ሰው የመባል ምኞቱን ተቀበረ.....
በራሱ መከራ..... ራሱ መከረ።
«በቃኝ» አለ..... «ደከምኩ» አለ
ላያይ - ላይሰማ - ከስቃይ - ከመከራ - ተከለለ
ራሱን ቀየረ? - መስል ሰጠ ለራሱ
ብሎ አፈር በላዩ........ አልብሱ
እሱ ነው አለ...... የአንዳንድ ሰው ዕድል ጉርሱ።
ብባል - እንጂ....... አፈረ
የሚል አይኖር ዋ!...... ያ! ሰው አለፈ!
ብሎ......
ማስኖ...... ማስኖ
ከርሞ..... ከርሞ
ታሞ...... ታሞ
ያ! ሰው አረፈ ደከሞ።
እንዲህ ሆኖ ለኖረ...... እንዲህ ሆኖ ላለፈ
ምነው ታዲያ...... እንባ ለእንባ ተላለፈ
አገር - ለአገር...... አገር - በአገር - ተላለፈ?
ችግር በእርሱ አድማ
በጐጆው..... ከትማ

የሩቅ በሩቅ ጠልቶት
የቅርቡ ሰው ርቆት
ዘመድ አዝማድ በቅቶት
አብሮት ያለው ታክቶት
አፈር....... ጭቃ...... ትቢያ!
ኤጭ!...... አሁንስ...... ወዲያ!
ተብሎ......የዋለ
ተገፍቶ..... የተጣለ
ለወደቁ..... ከፍቶት.....
ለአረፈ ሰው ደከሞት
ምን ሆናችሁ ሰዎች? ምን አሳዘናችሁ?.......
ምን አስለቀሳችሁ? የሞተ ሰው ቢሞት?
ብሶቱ....... ምሬቱ
ስቃይ...... እንግልቱ
ትላንት..... እንጂ ሞቱ
የቁም ሞት የሞተች....
ያረፈች ሕይወቱ
ዛሬ በዕረፍቱ ቀን
ምንድን ነው መንሰቅሰቅ
ምንድነው ሰቀቀን?
ደከሞት ለአረፈ ሰው......

እ...... ፎ..... ይ  ብሎ ላለ
መኖር ለታከተው......
ለተገላገለ
ምንድነው ቱማታ ምንድነው ዋይታ?....... ምንድነው ጫጫታ?
እንደተበደለ?
ንፍገት ባሚጠጠው.....
ለፍቶ ግሮ መና
ንቀት በገሰሰው
ክብረ - ስብእና
ሳያጣ ባጣ ቤት......
በሃዘን ገበና
አንጀቱን በአንጀቱ......
በብሶቱ ቋጥሮ
ባዶ ቤት...... ባዶ አንጀት......
......እሱነቱን ቀብሮ
ገበና ሚስጥሩን.....
.....ሕሊናው ነግሮ
ቢሆን ብሎ ጥሮ
አልሆን..... ብሎት ኑሮ
ባልሞተ...... ስሜቱ
ባልቆረጠ..... አንጀቱ

ባልታከተ ጉጉት....

በታከተ «ዕድል»

እስቲ «አንድዬ» ያውቃል እያለ ሲማፀን.....

ራሱን ሲሸነግል

በራስ እልህ እሳት......

ሲቀቀል ሲነፍር

«ድፍት» ብሎ ውሎ.....

«ድፍት» ብሎ ሲያድር

ማን አዛኝ አገኘ?.....

ማን ሰው ደረሰለት

ማን ችግሩን አየ?......

ማን ቁራሽ ጣለለት?

ለይምሰል ካልሆነ.....

ዋይ ትላንት አለፈ

«ይብላኝ»! ይብላን! እንጂ

የሞተስ አረፈ።

ዋይ! የት - ትሄዳለህ?......

«ወግ» ነው ከተባለ

እሪሪ! በፊት ቀሪ.....

ድሮ ነበር ሳለ።

አፈር መሬት ጭሮ

ከላይ እታች ግሮ
ከታች እላይ ጥሮ
አልሆን ላለ ሕይወት.....
ለታከተ ኑሮ
ምን ያሻዋል ለቅሶ?
ጐሽ እንዲያ ነው እንጂ!...... ሰሌን ቢጤ አብልሶ
አፈር መሬት ምሶ።!
ይልቅ ይብስ ነገር የባሰ ሣይመጥ
ሁሉም በነግ - በኔ
«በራስ» ብሎ ይውጣ።
«ወጊድ!» ይበሉ ሁሉም......
ሁሉም በነግ - በኔ
«በራስ» ብሎ ይውጣ።
«ወጊድ!» ይበል ሁሉም.....
«መወገዱ» ይብቃ
ከተጫነው ጫና.....
ከተኛበት ይንቃ
በሰው..... በተፈጥሮ.....
በራስ ሕይወት ያምጽ
ቋጥኝ አፈር ምሶ...... ነዶ..... ንዶ...... ያንጽ
የሃዘን ምሬት ኑሮ.....

ከዕንባ ፍሳሽ ሕይወት
በደም...... ጥረተ..... እንጂ
በዕድል አይታበት።
አለበለዚያማ......
ዕንባ ምን ሊፈይድ
ለማንስ ምን ክሶ.....
ማንንስ ሊገይድ?
ከቶም ትንፋሽ ላጣ...... ትቢያ ለለበሰው
አፈር ለነከሰ..... ቋጥኝ ለተጫነው
ተስኖት ላረፈ...... ጨርሶ ለተወው
አዬዬ!! ምን ሊያደርግ ከቶ ምን ሊሆነው?
ያን...... ሙት አካል ገላ.....
ዳግም ላይመልሰው።
.....ኖሮ ምን ለሌለው
...... ሞቶ ምን ሊቀረው?
....... ዋይ! ምን ሊፈይድ...... አንዴ ለታበተ
ለቀሪው ካልሆነ.... «የሞተማ - ሞተ»

# ማን ይደፍረው ነበር (1965 - ይዘት)

የአያ - ገበሬ «አህያ» ቡላ ከቤት ጠፍቶ
ቢፈለግ - ቢታረስ - ቢታሰስ - ቢፈለግ......
.....ቀኑን ሙሉ ታጥቶ
ፈላጊውም ገባ.....በውሎው ሰልችቶ
አያ - ገብሬም አዝነው ቡላ በመጥፋቱ
ሲበዛ..... ሲበዛ በጣም ነው ተፀፀቱ።
«አንድ እርሱ ቢኖረኝ
እውን ቡላ ቆርጦ ጠፍቶ ጉድ አረገኝ?
ኧረ - ኤዲያ!...... አሉ..... በቆረጠ ተስፋ
ይሂዳ! ይጠረግ!..... አስር ጊዜ ይጥፋ
ይሂዳ!..... ይጠረግ!.....
ዳግም ላንገናኝ ለቡላ ማደግደግ!!»
ብላው እርግፍ አረግው...... ሁሉን ነገር ተወት
ቢለኝ እሰየዋ!..... ቢሻው ይቅለጥ አሉት
በኋላ - በምሽት
በውድቅተ - ሌሊት
ቡላ - ከጅብ ሊያመልጥ
ሃ! ሃ! ሃ! - እያለ ሲሮጥ

ጅብም - ሲገሽልጥ
ቡላን ሲዘረግፍ..... ቡላን ሲዘረጥጥ
እሱን እንደቋንቋው አውው!! አውው!.....
......እያለ ሲቀብጥ
«የአያ - ገበሬ» ገላ - ስሜቴ ሚስቲቱ
ከእንቅልፋቸው ባነው - ወይዘሮ ደሚቱ
ከአንገታቸው ቀንተው - ትንፋሽ ሳይወጡ
ጆሮአቸውን ልከው ከሩቅ ቢያዳምጡ
ቡላ አስጥሉኝ ብሎ - የነፍሱን ሲጣራ
ጅቦም ሲገሽልጥ - የሆዱን ሲያጓራ
ሲጮሁ - ሲንጫጩ - እንደየ ቋንቋቸው
በተራ - በተራ በአንድነት ሰሟቸው።
ደሚቱም ደንግጠው
የቡላቸው ሃዘን - ዘልቆ ከአንጀታቸው
ቶሎ ብለው ዞረው...... ወደ «አያ - ገብርዬ»
አያ - ገብሬ!..... አያ - ገብሬ! አንቱዬ.... አንቱዬ
የመላኩ ያለህ!..... አይሰሙም..... አንቱዬ?
እያሉ..... ቢጣሩ..... ቢጐነትሏቸው
«ገብርዬ» ማን - ይሙት ደንታም - አልሰጣቸው።
ለካስ «አያ - ገብሬ» - ከጅምሩ ድሮ
ከእሜቴ ደሚቱ - ቀድመው ሰምተው ኖሮ

«ምንድ - ነው የምትይ..... ዛሬ ምን ሆነሻል
በእኩለ - ሌሊቱ - ምን ዛር ሰፍሮብሻል?
ምን ይቺ......» ብለው ሳይጨርሱ
የተቀላቀለውን ከንፈር ሳይመልሱ
«ኤጭ - ኤዲያ!» - ዘላለም ይኸው ኖት
ይልቅ ይነሱና ቡላን አንድ ይበሉ
ከጅብ ተያይዞ - ተጋድመው አይዩት
ብለው.....
ለጥ አሉ ደሚቱ..... ዳግም ተመልሰው።
ይቺ ነች «ገብርዬ» ይቺ ሰው ምን ሆነች
እንዲያው «ቢተው» ይሙት..... አጅሪት አብዳለች
ምነዋ ደሚቱ - ዛሬ ምን ሆንሽብኝ
ደሞ ብለሽ ብለሽ - ከጅብ ታማልጂኝ?
በሞቴ ንገሪኝ......
እንዲያው በምን ቋንቋ
በምን አዘመድሽኝ?
ቡላስ ይሄንን ሲያውቅ...... ድሮ ማንሂድ አለው?
ሮጦ ወይ ተራግጦ..... ራሱን ካላዳነው
ጅልሽን ፈልጊ - ይዘርጥጥ ያንከተው!!»
ብለው.....
ግልጽ አቋማቸውን ለደሜ ተንፍሰው

ጥቅልል አሉ ገብሬም «ጅላጅሎች» ብለው
　　　አሁንም ደሚቱ.... በንዴት ተነሥተው
　　　የሚያደርጉት ሳይሆን..... የሚሉት ጠፍቷቸው
«ኧረ..... እንዲያው ማ - ማ - ማ - ማን ይሙት
እውን አሁን እርሶ - በሞቴ «ወንድ» ኖት?
ቡላ እንኳን እንዳቅሙ - ሲታገል እያዩት
«አንገትን» አንጠልጥለው - ያንከተው የሚሉት?
ኤጭ - እቴ!..... አሁንስ ታዘብኮት
ደስ ይበሎት ይኸው...... ቡላ ተባብሎት......»
　　　አሉ.....
　　　እሜቴ ደሚቱ - እንባ እያነቃቸው
　　　ቡላ ደህና ሰንበት ብለው ከአንጀታቸው
«ሆ - ሆይ! ይኸውላችኋ! - ድሮ አልቀረልኝም
ይቺ ሰው አብዳለች - እኔ አላልኳችሁም
የዘራፍ!! የጐራው!! የወንድ ወንድነቱ
የሰውነት ሚዛን የተግባር ውጤቱ
አንቺ ባልሽ «እንጥልጥል» ምኝኖት የሚረካ
ቢሆንማ ኖሮ «በእንትን» የሚ'ለካ
ደሚቱ!.....
　　　ማን ይፍረደው ነበር..... ቡላን ማን...... ሊነካ?

# «ወይ - ዕዳ» (1976 - ገጠመኝ)

ሳላነጋግራት..... ሳላውቃት..... ሳታውቀኝ አ
አይቻት..... ሳታየኝ...... ሳትነነጋግረኝ
ምላስ አንደበቷ...... ቃላት ሳይተነፍስ
ያናገረኝ ዓይኗ..... መንፈሴን የሚያምስ
ገላጋይ ላይገኝ የሰው ጭንቀት ሰሚ
እኔን የሚል ላይኖር...... የችግር ቀዳሚ
በመንገድ ላይ ጉዞ...... በቀን አጋጣሚ
ሸመትኩኝ ለልቤ...... ስውር ተፋላሚ
በመንገድ ላይ ጉዞ.....
.....ከአውላላው ከሜዳ
ከቀን አጋጣሚ.....
......ከማይሆን እንግዳ
ከመስከረም አደይ.....
......ከዕንቡጥ ጽጌረዳ
ወይ ዕዳ!!..... ወይ ዕዳ!!
ከመንገዱ ዳር..... ዳር.....
......ከጠርዙ - ከጠርዙ
ከለጋው ዘንባባ.....

.....ከአክርማ ሰበዙ
የልቤ መዘዙ..... የልቤ መዘዙ!!
እከሊት ሳልላት....... ሳትለኝ እከሌ
ቃል ሳትተነፍስ....... ሳይሰማኝ ቃሌ
አይቻት ባየችኝ...... ከመንገድ ከጠርዙ
ለሁለንተናዬ...... ተረፈ መዘዙ።
ውሎ ማደሪይዋን..... ስፍራዋን ሳላየው
የባህል ልማዷን..... ቋንቋዋን ሳላውቀው
ዓይኔ ተወርውሮ...... ዓይኗን ስለቃኘው
አንዳች ነገር ደርሶ..... አንጀቴን አመሰው።
ሰዎች...... ለነገሩ
ምን ይሆን? ሚስጢሩ?
ተናግሬ አናግራኝ...... ቀርባኝ ሳልጠጋት
ሰላም ጤና ይስጥልኝ....... ሻይ ቡና ሳልላት
የስሜቴን ምስጢር....... ውስጤን ሳላሳያት
አንጀቴን አውጥቼ...... ልቤን ሳልጋብዛት
የጥንተ ታሪኬን...... ወጌን ሳላወካ
ትኩስ አፍላ ደሜን...... በደሟ ሳትለካ
አካሏን አካሌ...... በአካል ሳይዳስሰው
ስሜቴ ስሜቷን...... ዘልቆ ሳያምሰው
እንዳረርኩኝ አርራ..... ነዳ ካልነፈረች

እሷም ከእኔ ብሳ...... ካልተብጠለጠለች
አሁንም አንተዬ...... አንተዬ..... አንተዬ..... አንተዬ ካላለች
እንዲያው በራስ ስሜት.....
        በአካል ብሌን ቅሉ
ይኮናል ወይ ዞፉ.....
                ያሻል ወይ መቄሉ?
        በመንገድ ላይ ጉዞ......
ከቀን አጋጣሚ......
        ከማይሆን እንግዳ
ከመስከረም አደይ......
        ......ከዕንቡጥ ጽጌረዳ
ወይ ዕዳ!!...... ወይ ዕዳ!!
        ከጠርዙ ከጠርዙ
ከለጋው ዘንባባ.....
        ......ከአክርማ ሰበዙ
የልቤ መዘዙ...... የልቤ መዘዙ!!

..........

........................

.......................................

# እናት - ሃገር (1974 - ዜግነት).

ከዘመናት ዕብሪተኞች ልብድ ሾተል
ከዘመናት ሞገደኞች አፋፍ ገደል
ከዘመናት በደለኞች የግፍ በቀል
ከአካል ክፋይ ገፋፊ ከሥጋ ቁራጭ አረመኔ
ከታሪክ ትፋት ወያኔ
ከአልጠግብ ባይ ስግብግብ ከአያሌ ዘራፊዎች እሚግተሽ
ከአዕዋፍ ሰማይ ሰው በላ ከወራሪ ፋሽስት ተፋጨሽ
ከወደቀው ልጅሽ ወድቀሽ
በወደቀው ልጅሽ ፀንተሽ
የዘመናት ሰው ሰራሽ ተንኮል የተፈጥሮን ችግር ተቀብለሽ
ለልጆችሽ ጥላ ከለላ በእናትነትሽ ጋሻ ሆነሽ
ያፈራሽው የዘር ፍሬ አካል ብለሽ ያሳደግሽው
የማህፀንሽ ሥጋ ቁራጭ ልጄ ብለሽ የጠራሽው
የክፉ ቀን ተጠሪዬ አለኝታዬ ክንዴ ብለሽ
ለሕይወቱ ሕይወት ሆነሽ
ያመንሽው ልጅ የአካል ክፋይ ከቶም ጠላት ሆኖ ሲሸሽ
የጥቃትሽ በር ከፋች ጦር ሰባቂ ሲሆን አየሽ?
አረንጓዴ ለምለም መስክሽ

ወንዝ ጅረት ፈሳሽ ምንጭሽ
እሹሩሩ ያለው ጀርባ የእናት ፍቅር የእናት ጡትሽ
በግል ጥቅም ሲረታ
እናት ዓለም ተመለከትሽ በከሃዲ ልጅ ሲመታ?
በበስባሽ ሥጋ ቁራጭ
በመርዘኛ የደም ዝቃጭ
በመሰሪ ስሌት ዘዴ
በወራዳ ታሪክ ውርዴ
ለእናትነትሽ ወሮታ
ለማጎፀንሽ - ማጎደር ትዝታ
ንክሻ ሆኖ ብድሩ
ክህደት ሆኖ ምግባሩ
ክፉ ቀን ሆኖ ሲያስከፋሽ
ባላንጣ ሆኖ ሲያደማሽ
ወራሪ ሆኖ ሲድክሽ?
ቅጥረኛ ሆኖ ሲክድሽ?
ከቶ ምን ይበል አንጀትሽ?
የእናትነት ፍቅር ስሜትሽ?
እናት ሃገር!
የጥንተ ታሪክ ቅርስሽ
የነፃነት ክብር ውርስሽ

የተተኪ ትውልድ አምሳያ
የታሪክ ተረካቢ ቡቃያ
ለጋ ሕይወት ለጋ ቁመና
እንቡጥ እሸት በሳል ቃና
የሃገር ፍቅር የሃገር ዓርማ
የሃገር ቋንቋ - የሃገር ማማ
በወንበዴ የጥፋት ተልዕኮ......
.....በጥቅም ወረርሽኝ ልክፍት ዱካ
እናት ሃገር ተመለከትሽ በጣዕረ ሞት ሲቃ...... በዋይታ ድምፅ ሲተካ?
የሰላም ጉጉት ድምፅ ጥሪ
የለጋ ሕይወት ደማቅ ዓለም
በደስታ ፈንታ ሃዘን በምጽዓተ ስቃይ ሲታለም
የታዳጊ ሕይወት ብሩህ ተስፋ በሽብር አደባባይ ሲጨልም
የእናት አገር የዘር ፍሬ በከሃዲያን እሳት ሲቃጠል
የጀግኖችሽ ክብር አጸም የወላደ አንጀት ምን ይበል?
በግፈኞች የግፍ ስለት ለጋ ሕይወት ሲሰየፍ
የእናት ሀገር ክቡር ታሪክ የወላድ አንጀት ምን ያትርፍ?
እናት - አገር!
በከንቱ ዓላማ ውርዴ በታሪክ ወራዶች ዲቃላ
በሰላም አጥፊ ቅጥረኛ በትውልድ አስወቃሽ አተላ
የእናት ዓለም ክብር ማዕድ

የልጆችሽ የልጅ አንጀት በረሀብ ሾተል ሲሰረጐድ
በእናት ቋንቋ - በእናት ፍቅር
በእናት አገር በእናት ምድር
ጥማት እርዛት ስቃይ ውርደት
ጐጆ ዘግቶ ዞሮ ስደት
በልጆችሽ ሕይወት ሲደሰት
የጥንተ ጥንት አኩሪ ታሪክ የቆራጥ ልጆችሽ ሃቅ ማኅተም
ለአንድነትሽ ሕልውና ለሕዝቦችሽ ብልጽግና የወረደው የደም ቀለም
ምን ይል ይሆን እናት ዓለም! ምን ይል ይሆን እማማ!
ይህን ክህደት - ይህንን ሽፍጥ ቢሰማ?
እናት - ዓለም
የወሮ በሎች ውሎ ይህ ቢሆንም
የአካል ምድርሽ ፍላጭ ክፋይ
የክቡር ማህፀንሽ ዝሬት ብቃይ
ጥቃትሽ ቆሞ ላያይ
ውድ ሕይወቱን ለሕይወትሽ
ደም አጥንቱን ለአንድነትሽ
ለክብርሽ ሲል ራሱን ሰጥቶ
ለታሪክሽ ድል አቅልቶ
በተራራው - በጅረቱ
በየፍልሚያው - ማዕዘናቱ

በየኬላው - በየበሩ
በአገር ዙሪያ በአገር ምድሩ
ይሰማሻል? አለሁ ሲልሽ
ይታይሻል? ጀግናው ልጅሽ
ጠንቀኛሽን በእህል አንቆ
«እናት - ሃገር»! ብሎ ወድቆ?
እናት ዓለም......
በተራ - ወንበዴ ሽፍታ
የታሪክ ውልሽ ላይፈታ
ሃቅ እውነትሽ ላይረታ
የድል ጉዞሽ ላይገታ
በቅጥረኛ «ወሮበላ» ግርግር
በአከክልኝ ልከክልህ ድርድር
ሕያው ታሪክሽ ላይገደል
የአንድነት ዋልታሽ ላይነደል
ጀግናው ልጅሽ ከፍልሚያው ጕራ ላያፈገፍግ
ሃቀኛው ልጅሽ ከትግል ሜዳ ፊቱን ላይሸሽግ
ቆራጥ ሕዝብሽ በጠላት ጉራ ላያደገድግ
ቃል ይገባል ለቃልሽ
ቃል ይገባል ለክብርሽ
ሕይወቱን ሊሰጥ ለሕይወትሽ።

ቃል ይገባል ለቃልሽ
ቃል ይገባል በስምሽ
ጥሎ ሊወድቅ ለአንድነትሽ።
ቃሉ በቃልሽ ሰምሮ
ቃል ለቃል ተነግሮ
ቃል በተግባር ተመስክሮ
ይኖራል ቃል ለቃል ተሳስሮ
ቃልሽ በቃሉ..... ቃለ - ውሳኔሽ..... በትግርሉ ተከብሮ።
እናት - ዓለም......
ከዚያ ወዲያ ግን..... በሃቀኛ ልጆችሽ ስም
በወደቁት ጀግኖችሽ ክቡር አጽም
በተሰው ልጆችሽ - የደም ማኅተም
ቃል ይግባልን ከእንግዲህ ወዲያ
ጀርባሽ ተናካሽ ልጅ ላይሸከም።
በጽኑ ዓላማ በእውነተኛ ስሜት ገላጭ ቃል
ጀግና ያፈራ ድንግል ማኅፀንሽ
የዓመተ - ዓመታት ክቡር ገድል
ቃል ይግባልን ከእንግዲህ ወዲያ
ምድረ ምናምንቴ ላያበቅል።
በጥንተ - ጥንት ተጋድሎ...... በአዲስ ታሪክ አዲስ ዘገባ
በሀቀኞችሽ ሕይወት ዕልፈት

በክቡር ዓላማቸው የደም አምባ
ቃል ይግባልን ከእንግዲህ ወዲያ......
ጡትሽ ከሃዲ ልጅ ላያጠባ።
ዓመት በዓመታት ተተክቶ..... ዘመን መጥቶ ዘመን ቢያልፍ
የእናትነትሽ ሩሁሩህ እጅ..... አረመኔ ልጅ ላያቅፍ
ቃል ይግባልን አንደበትሽ..... ቃለ ውሳኔሽን ላያጥፍ
ከዚያ ወዲያ ን......
ከትዕግሥትሽ ክልል ባሻገር...... ከበደልሽ እንባ ድቅን
ከውሳኔሽ ብቃት ማዶ..... ከቃልሽ ጽናት ወሰን
በድብቅ ዓላማ በግል ሽፍጥ ውንብድና
በእከከኝ ልከክልህ በእንካ ለእንካ ውክልና
በየጥሻው..... ተሽሎክልከው
በየጉድባው..... ተለጥፈው
በየጋራው....... ተንጠጥለው
በየጓዳው....... ተወትፈው
አይኖራትም ከእንግዲህ ወዲያ...... የእናት ኢትዮጵያ ደም መጠው
አይኖራትም ከእንግዲህ ወዲያ...... ሰፊውን ሕዝብ ሰላም ነስተው።
በሰፊው ሕዝብ ሐቅ ላይ ሸፍጠው
በሰፊው ሕዝብ ነፃነት ላይ ሸፍተው
የሰፊው ሕዝብ አንድነት ንደው
የሰፊውን ሕዝብ መብት ሸቅጠው

አይኖራትም ከእንግዲህ ወዲያ...... በእናት አገር ሕልውና ላይ አድመው
(የቀይ ኮከብ ዘመቻ መታሰቢያ - 1974)

## የደሜ - ደም - መላሽ (1967 - አመጽ)

ከጨቋኝ ሰንሰለት
እጅ እግሬን አላቆ
የግፍ ደሜን ፍሳሽ.....
.....እንባዬን አድርቆ
ለሰው ሰውነት ሰው....
.....ለድል የሚያበቃኝ
መራራ ትግሌ ነው.....
.....ነፃ የሚያወጣኝ።
ፈዋሽ መድሃኒቴ.....
.......የጥቃቴ ደራሽ
መራራ ትግሌ ነው......
......የደሜ ደም መላሽ።
የምኞቴ ወደብ......
......የግቤ መድረሻ
መራራ ትግሌ ነው.....

የዓላማዬ ጋሻ

የታሪኬ መዝገቤ.....

.....የደም ብቅለቴ ውል

የመኖሬ ተስፋ.....

......የሃቅ እምነቴ ድል

የነፃነት ክንዴ.....

......የጥቃቴ ደራሽ

መራራ ትግሌ ነው......

......የደሜ ደም መላሽ።

.........

.................................

.....................................................

.......................................................................

# የኔ ጋሻ (1976 - መስዋዕትነት)

በራስ አገር - በራስ ምድር
በራስ ሕይወት - በራስ ፍቅር
በራስ አምባ - በራስ እውነት
በራስ ቋንቋ - በራስ እምነት
ባዕድ ሆኖ - ባክኖ ቀሪ
ለራስ ሞቶ - ለአንዱ ኗሪ
ለራስ ጭልም...... ለአንዱ ተስፋ
እንዴት ሆኖ ሊከረም
እንዴት ሆኖ ሊገፋ?
የሚል - ሮሮ - ብሶቴ
የእህል እምቅ ቁጭት
የጉስቁልን ባካኝ ሕይወቴ
የጥቃቴ ጩኸት ሰቆቃ!
የጭንቀቴ እንባ ሲቃ!
የእንዴት አይሆንም - እልሄ!
የሰማዩ - ሰማያት..... - ምልጃ ኤሊሄ!
የባርነት ግርዶሽ ጽልመት
የመከራ ቀንበር ጭነት

እንክት ብሎ ሲወድቅ - ስንጥቅ ሲል ሰንሰለቴ
ነፃ ሲወጣ - ነፃነቴ
የአገር ምድር - የአገር ሰማይ
የአገር ሌሊት - የአገር ፀሐይ
የአገር ዙሪያ - ክቡር - አጽም
የኔ - ጋሻ...... የኔ - ወንድም
ባየሁህ ምነው..... ባየኸኝ
«እከሌ» ብዬ በጠራሁህ - «እከሌ» ብለህ በጠራኸኝ?
ምነው! ዛሬ ባየኸው
ውሎ አዳሬን ቢቃኘኸው!!
የሰው የመሆን ምኞቴ
የክብረ - ስብዕና ጉጉቴ
ጥሮ የማግኘት አምሮቴ
የማይጨበጥ - ባዶ - ተስፋ
በግፈኞች ግፊት - የተደፋ
በዕብሪተኞች ዕብሪት - የተገፋ
ለሰዓት - ለደቂቃ
በተፈጥሮ ስሌት ፈረቃ
በቀን ውሎ በጨረቃ
አቅመ - ጉልበቴ - ከአዋይ - ምድር
ጥረት ልፋቴ ከኔ ላይቀር

እንዲሁ ብቻ በሰው ምስሌ
በዕውን ሽፋን ባዶ - ቅሌ
ሲለገጥበት - ዕጣ - ዕድሌ
በተረት - ተረት - የላም በረት
ሲፌዝበት የኔ - ዕውነት
  በኔ - ወንድም....... በኔ - ጋሻ
  በታሪኬ - ማስታወሻ
  በአንተ ውሎ - በአንተ ትግል
  በአንተ ሕይወት...... ዕልፈት ገድል
ይኸውና - አገግሜ
በአንተ መሞት - እኔ ቆሜ
  ሽብብ - አንደበቴ - ተፈቶ
  ጭልም ተስፋዬ - ንጋት ቃኝቶ
  ጥውልግ ሕይወቴ - ሕይወት ዘርታ
  «ባዶ» ገበናዬ - «አዋይ» ሽታ
ብሩህ ዘመን - ብሩህ ፀሐይ
በአገር ምድር..... በአገር ሰማይ
በሁለንተናዬ ሕይወት አድማስ - ወጋገኑ ደምቆ ሲታይ
  «ጋሻዬ»! - ዛሬ ብታየኝ!
  ደስ! ቢልህ - ደስ! እንዳለኝ።
«ጋሻዬ» ምነው - ላንድ አፍታ

ለሰከንድ ዕድሜ ቆይታ
አንደበትህ ለኔ በተፈታ
የተጫነህ አፈር በተርታ!
አንደበትህ «እሰይ» ባለ
አይታይህ ለኔ - በታደለ
ምነው ለሰዓት ለደቂቃ
ለድል ዕለቴ ብትበቃ?
ዕምነትህ ሆኖኝ እውነቴ
ዓላማህ ሆኖኝ ጉልበቴ
ሞትህ ሆኖኝ ሕይወቴ
ሕሊናዬ - በትልምህ ረክቶ
ተስፋዬ - በትግልህፈክቶ
ነፃነቴ ለድል ሲበቃ
«ጋሻዬ» ምነው ብትነቃ?
የዕብሪትተኞች ዕብሪት ድንፋታ
በትግል ክንድህ ሲረታ
በደምህ ፍሳሽ ጠብታ
የባርነት ሰንሰለቴ ሲፈታ
ትግልህ በደል ሲነገር
ሞትህ በገደል ሲዘመር
የሩቅ ትልምህ ሀቁ ሲለይ

ቅን ዓላማህ ግቡ ሲታይ
«የኔ - ጋሻ» - የኔ - ሳተና
የኔ - ጐበዝ - የኔ ጀግና
ምነዋ! በል ብትነሳ
ሞትን በሞት ድል ብትነሳ?
ትግሉን በትግል የመለሰው
የዕብሪት ልቡን የደቆሰው
ቆራጥ ክንድህ ኃያሉ ሰው
አፈር መናድ መቼ ያቅተው?
«የኔ - ጋሻ» - የኔ - ወንድም
የእናት አገር - ክቡር አጽም
ይኸውና በአንተ ትግል
በሕይወትህ ዕልፈት ገድል
ቋንቋዬ ቋንቋ ሆኖ - የቃል ፍቺ ትርጉም ናኘቶ
አድማጭ - ሰሚ - ወግ - አግኝቶ
ከኔም አልፎ የኔ ሕይወት - የሀገር ሕይወት ሰው ተብዬ
ሃሳብ ሰጥቶ ሃሳብ መውሰድ - መናገርም ይኸው ችዬ
የሕይወትን ድብቅ ሕይወት - የፍጥረትን ሚስጢር አየሁ
ሁሉን ነገር አስተዬ - ሁሉን ነገር በውል ለየሁ።
«ሀ» ማለትም መልካም ሆኖ - ማወቅ ደጉ ጥሩ እንነገር
ሰማይ ምድሩን ሽፍን ዓለም - ደም - መናውን አየው ጀመር።

በእናት ምድር በዚች አምባ
ያሳለፍኩት የሕይወት ሚስጢር - ያፈሰስኩት የግፍ አንባ
እሳት ቋያ መብረቅ ሆኖ - ጥንብ አሰሉን ገረሰሰ
የአገር ጩኸት አገር ሰምቶ - ለአገር ሕይወት ደረሰ።

የአገር ምድር - የአገር ሰማይ
የአገር ጀንበር - የአገር ፀኖይ
የአገር ዙሪያ - ክቡር አጽም
«የኔ - ጋሻ» - የኔ - ወንድም
በአንተ ዓላማ - በአንተ ትግል
በሕይወትህ ዕልፈት ገድል

የሕይወቴ ሕይወት ማህጸን
የትውልዴ ዕድገት ዕርከን
የነፃነቴ ምንች ጉልላት
ክብሬ - ካባዬ - የምላት

ልጄ ክንዴ የምትል - የአንድነቴ ጋሻ መከታ
የታሪኬ ሐረግ ድርና ማግ - የሕልውናዬ አጥር አለኝታ
በእናትነቷ የኮራሁ - በልጅነቴ የኮራች
በልጅ ልጅዋ - ደም የጻናች
እኔም የሀገሬ ሀገሬም ይኸው የኔ - ሆነች።

ውበቷ በውበት ስሜቴ ሊደነቅ
ክብሯ! በአጥንቴ ክስካሽ ሊጠበቅ

ሕይወቴ ለድል ሕይወቷ ሊሰነቅ
ይኸው - ዛሬ
በሐቅ ዕውነታ በደም ፍሬ
ሀገሬ የኔ ሆነች - እኔም ሆንኩላት የሀገሬ።
«የኔ - ጋሻ» - የኔ - ወንድም
የእናት - ዓለም - ክቡር - አጽም
የታሪክ ሐቅ - ዕድገት ቅምር
የዓላማ ደም - ሕይወት ድምር
የሩቅ ጉዞ አለኝታዬ ሐቅ አብሳሪ ሀቅ አላሚ
የጥቃቴ ጋሻ ምክት - ሊድል ግቤ ተፋላሚ
የአገር ምኞት - ሕያው ድርሳን
የመራራ ትግል ክንዴ - የወል ቋንቋ የወል ልሳን
ክልል አልባ - ተጓዥ - ማዕበል
የዓላማዬ መሪ «ማዕበል»
ይኸውና - በአንተ ውሎ - በአንተ ትግል የደም ፍሬ
ሕያው መልኩ ታዬ ዛሬ!
በአንተ ዓላማ - በደም ልምህ
በአንተ ትግል - በሞት ገደልህ
ይኸውና «ሰው» ሆንኩልህ
«ደስ» እንዳለኝ «ደስ» ይበልህ።
«የኔ ጋሻ» - የኔ - ወንድም

የእናት - አገር - ክቡር አጽም
ለኔ ስትል - አንተ አልፈውኸው
አፈር ትቢያ - የለበስከው
መከራዬን - በእንተ መክረህ
የቁም ስቅሌን - ሞቴን ሞተህ
ጋራ - ቋጥኝ - የተጫነህ
አፈር - ትቢያ - የተበየህ
በእርግጥ ሞቴ - ሞትህ ሆኖ
ጽልመተ ሞት - በእንተ ሰፍኖ
ዓይነ ውሀህ - በውል ቢፈስ
አካል ገላህ - አፈር ቢለብስ
ቋንቋ ሆኖ - «ባሕለ -ሰው»
ሕሊናዬን አጽጽቼ - ሞትክን «ሞት» ነው ማለት ባልተው
የአንተ ዓላማ ዓላማ - የአንተ ዕምነት
የአንተ መድረክ - የአንተ ዕውነት
ቋሚ ታሪክ - ቋሚ ሰንደቅ
ያልሞተ ሰው - የማይሞት ሀቅ
የአንተ ትግል - የአንተ እልፈት
ሕያው ታሪክ - ሕያው ሕይወት
ፀጋ - ክብር የኔ - ሽማ
የአንድነቴ ሕይወት ማገር - የነፃነት መቅረዝ ሻማ

መሆኑንስ መች አጥቼ - የታሪክ ምንጭ ባሕር ቅኟ
የሀገረ - ሰብ ቋንቋ ሆኖ - ሞትክን ሞት ነው አልኩት እንኟ!
የኔ - ወንድም - «የኔ - ጋሻ»
የታሪኬ - ማጣቀሻ
«እጅ እግርህ...... እንኟ...... የታበተ
የትግል ክንድህ..... እንኟ...... የታከተ
አቋም ውበትህ...... እንኟ...... የተከተተ
በአፈር በትቢያ...... የተነከተ
የትግል ሕይወትህ እንኟ የጐመራ
የሩቅ ትልምህ እንኟ የበሬ
የደም - ፍሳሽህ እንኟ ድል የመራ
ሐቅ እውነትህ እንኟ የደራ
ሀቅህ እንኟ ሀቅ ያደለ
ትግልህ እንኟ ታገል ያለ
ገጸ - ውበትህማ የታለ?»
በሚል እምነት የምታበል
ብዬ ሳይሆን የምታገል
ሕይወቱን በሞት የሚያልም
የታበተ ክንድ የተከተተ ውበት የለህም
ክንድህ በክንዴ ተተክቷል
ውበት ግርማህ - በአገር ለምቷል

ብዬ ነው እኔ የማምን
ትግሌ በድል የሚሰክን።
የአገር ምድር - የአገር ሰማይ
የአገር ድንበት - የአገር ፀሐይ
የአገር ዞሪያ - ክቡር አጽም
«የኔ - ጋሻ» የኔ - ወንድም
መከራዬን በአንተ መክረህ
የቁም ስቅሌን ሞቴን ሞተህ
ጋራ ቋጥኝ የተጫነህ
አፈር ትቢያ የተበየህ
በእርግጥ ሞቴ - ሞትህ ሆኖ
ጽልመተ - ሞት - በአንተ ሰፍኖ
ዓይነ ውሀህ በውል ቢፈስ
አካል ገላህ አፈር ቢለብስ
የአንተ ዓላማ - ላፍታም አይፈርስ
ንጹሕ ገድልህ አይደፍርስ!
የኔ - ወንድም...... «የኔ - ጋሻ»
የታሪኬ - ማስታወሻ
ጅምር ትግልህን በትግል..... ትልምህን ከግብ ላደርሰው
ገድልህን በገድል ላድሰው
ሞትክን በሞቴ ልክሰው

እኔም ሕይወቴን ልሰንቅ
የድል ግኝትክን ልጠብቅ!
ከሩቅ ጉዞ ከመንገዱ
ከትግል ቋያ ከንዳዱ
«ጋሻዬ እየኝ - ከመስመሩ
ቆሜ ስፋለም ከግንባሩ?
«ጋሻዬ» እየኝ - ከመድረኩ
በየኬላው በየመስኩ?
ሀቅህ በሀቁ ይቀሰቅሰኝ
ሕያው ታሪክህ - ይታዘበኝ
ዓይነ ሙታንህ - ይመልከተኝ
«አላማህን» የወረስኩ «ጋሻህን» ያነገብኩ እኔ ነኝ።
የአኩሪ ታሪክህ የክብር ዘብ...... የዓላማህ ብያኔ ቃሉ
እኔ ነኝ የአንተ ዕውነታ..... የደም ግኝትህ ሀቅ ስምሉ
እና.....
ይጠየቃል!! ይከበራል ይከበራል!! በደሜ! የደም ሰነድ የደም - ውሉ።

10ኛው ዓመት የኢትዮጵያ ክብር በዓልና የኢ/ሠ/ፓርቲ ምስረታ ምክንያት በማድረግ በተዘጋጀው ሃገር አቀፍ የኪነ - ጥበብ ውድድር የግጥም ዘርፍ አሸናፊ

## ያን ዕለት ሞት ይሙት (1974 - ፍጻሜ)

ዕልፍ..... አዕላፍ ጦረኛ
ዞር.....ጥምጥም...በረኛ
ሕንፃ የማይከልለው..... ኑክለየር የማይገፋው
የተዳፋች ጐጆ...... ደረባ የማይከፋው
ለብረት መሰሶ...... ለሸንበቆ አጥር
ልቡ እማይሰብር የማያቀረቅር
በመራራ አንደበት.....
......በጣፈጠ ልሳን
በአመዳም ጭርንቁስ.....
ወርቀ ዘቦ ዙፋን
የሚያሽቆለቁል..... ከቶ የማያሽቅብ.....
.....ለፍርዱ ቀን ሚዛን
ሞት - አስተካካዩ
ሞት - አደላዳዩ
ሁሉ - አደባባዩ
የሁሉ - ጓደኛ
እከሌን በእከሌ..... እከሌን ከከሌ..... ብሎ የማይል ዳኛ
የፍትረጥ ዘር ጠላት.......
ቀድሞ ማሽለቡ....

ሞቱ ለማን ይበጅ?
የደም ዝውውሮሽ......
.....የልብ እብጠት ልፋጭ
የዘር ማንዘር ልክፍት.....
.......የቆዳ - ሰብ እባጭ
ሞገድ የሞገደው.....
......አግድም አደግ ስላች
ከፍጥረት ደመ - ነፍስ
.....ከሰው የሰው እኳች
ፈልፈልቱ መሰሪ.....
«ረገምት» የረገመው
ውለናም ጭበኛ.....
ቅንቅን የወረሰው
በሽተኛ እያለ.....
ታሪክ ያገለለው
በቋሚ ሚዛኑ በቀኑ የሚታመን
ሞትን ለሞት መዳን መጋበዙ ለምን?
የሰላም ጠንቅ ጦስ ዕብሪት ቆሞ ሳለ
ሞትም አብሮኝ ይሙት ሞት ይሙት ተባለ?
ጭካኔ ካልሆነ ወይ እንዳይሆን ታልፎ
ሞት እንዴት ይሞታል? አሽከላ ወዝፎ?

ሃጅ ወጪ ከሆነ.....

......የዘወትር እንግዳ

የዕድሜ ሃዘን አማጭ.....

....የሕይወት ጣር ፍዳ

የማይቀር ዳኘነት.....

የተፈጥሮ ዕዳ

ሟች - ተቀባሪውን.....

.....በቁም ሞት ገንዞ

ከመሞቱ በፊት.....

....ሞት ሞትን አርግዞ

እነዚያ ቆራጦች

ቅን ሰዎች አሟጦ

ከፍጻሜው ሥፍራ......

በክብር አስቀምጦ

ለመልካም ሥራቸው....

ለቁም ነገር ዛላ

ከአስተናገዳቸው......

....ከሸኘ በኋላ

ያን ዕለት ይጨፈር...... ሞት ተብሎ ሞተ

ሞትም «የት - አባቱ»..... በተራው ታበተ።

ፀሐይ ከንክርቷ.....

ከንብርቷ ስትለቅ
እስከ ዘላለሟ.....
ለሁሌ ስትጠልቅ
በሕህዋው ዓለም ላይ.....
ዳግም ላትሰቀል
የዓለምን ምጣኔ....
ፍቅር ላትቀበል
በጨረቃ ግርዶሽ.....
ከቶ ላትከለል
በነዳዲ ጨረሯ.....
ፍጥረት ላትበቀል
አሽቆልቁላ ወርዳ.....
ከአለት ጋር ስትፋጭ
ከተፈጥሮ ደንቦች.....
ከህጎች ስትጋጭ
ያ - ሃያል ንዳዷ.....
ቃጠሎው ሲደክም
እስከ መጨረሻው....
ዝንተ ዓለም ሲጨልም
ዳግመኛ ላይበራ.....
ለሁሌ ሲከስም

ሁሉ ነገር ሞቶ..... መኖሩ ሲታጣ
ያን ዕለት ሞት! ይሙት የሚገለው ሲያጣ።
ምድር ስትመክን......
        ሲቆም ግልጋሎቷ
በያለበት ሲከስም.....
        ሲጠፉ ስበቷ
ለፍጥረት ዘር ያላት.....
        ስጦታ በረከት
የማህፀኗ ፍሬ....
        የተፈጥሮ ለከት
ያዘለችው ፀጋ......
        መልካም ደግ ነገር
በዘላለም ጥፋት......
        በጽልመት ሲነከር
ቃጠሎ ንዳዱን.....
        የጋዝ ጢስ ስትምግ
የእናት ምድር ጡቷን.....
        ወተቷን ስትነፍግ
ይደለቅ ከበሮ..... ለፍጥረት ይነገር
ሞትም የታባቱ..... ያን ዕለት ይቀበር።
የጨረቃ ድምቀት....

ብርሃን አብቅቶ
የወፎች ዝማሬ.....
ሸጋ ጣዕም ጠፍቶ
ጉበዝ በተፈጥሮ.....
በህጎች ሲረታ
የአዲስ ነገር ምንጩ.....
ሂደቱ ሲገታ
የሰው መልኩ ቀርቶ.....
ስሙ ላይነሳ
የታሪክ ዓለሙ.....
ውሎው ላይወሳ
ተደናቂ አድናቂ......
ጠፍቶ ሲረሳሳ
የፍጥረት ዘር ችግር.....
በለመለመበት
የተፈጥሮ ሕጉች.....
ዱላ ሲወርድበት
በሰው ልጆች ኑሮ......
በውብ ዓለም ድምቀት
እሳተ ጉሞራ.....
.....ቁጣ ሲወርድበት

ቀዝቃዛ በረዶ.....
ውሃ ሲፈስበት
ያን ዕለት ሞት ይሙት.....
.....እሱም ይፍረድበት።
ከኢምንቷ ቅኝት......
ከደቃቋ ነፍሳት
ከአራዊት መንጋ.....
......እስከ ዝሆን አባት
ከቡቱቷም ድሃ....
......ለማኝ ቁራሽ ጉርሱ
ከጠገበ ፈርሳም.....
...... እስከ ብር ትራሱ
ከሰው ዘር ቤተሰብ.....
.....ከስልጣኑ ፈሰስ
ከሰፈር ሹመኛ.....
እስከ «እግዜሩ» ንጉስ
ከጠቢብ ባለሟል.....
....ከሊቅ እስከ ደቂቅ
ለሩቅ ህይወት ዓለም.....
.....ለቆይታ ተስፋ
በየሙያ ዘርፉ ለኑሮ ሲዳፋ

አለሁ ብሎ ሲኖር.....
ለመኖር ሲለፋ
የዘላለም ዕድሜ.....
....ሲጠቅም ሲሰፋ
በያለበት ሲቀር.....
.....እዚያው ሲያንቀላፋ
የደመ - ነፍስ ዕድሜ.....
..... የሩቅ ጮራ ሲያልም
በተፈጥሮ ምጽዓት.....
.....ተፈጥሮ ሲጨልም
የፍጥረት ዘር ውሎ.....
.....ቆይታ ለመይቴ
ዳግም ላይ ነደፍ.....
.....ላይፃፍ አብቅቴ
ግጥም - ጥም - ሲል......
......ሁሉ ነገር ሲቆም
የህይወት እስትንፋስ.....
.....«ትንሣኤ» ሲያከትም
ሁሉም በያለበት...... «በጉድ - ጉድ» ሲወጣ
የድንገት ፍጻሜው..... ከተቱ ሲመጣ
ያን ዕለት ሞት ይሙት..... የሚገለው ሲያጣ።

..........

..............................

...................................................

.....................................................................

## ልቤ - ከእኔው ጽና (1967 - ወዳጅና ጠላት)

ናፍቀህ - የናፈቀህ
ብታስብ - ያሰበህ
 ብትወድ የወደደህ - ወዳጅ የለምና\
 ከርታታው ገንዘቤ - ልቤ ከእኔው ጽና።
ለወደድከው ወዳጅ ለፍቅር ያደርህ
ለአመነህ ሰው ታማኝ ልቤ ሟች ነበርህ
ታዲያ ምን በወጣን ማን ብለህ ትጐዳ
ስትቀርበው በሚርቅ ስታምነው በከዳ?
ስታስብ ለረሳህ እያየህ ላለፈ
ንፁህ ማንነትህ በከጂ ከአደፈ
ለአፈቀርከው - ፍቅር ለወደድከው መውደድ
ምላሽ ካላገኘህ - ለመንገድህ መንገድ
መሰልህ ከጠፋ - የሚቆይ አምነኸው

ብቻህን መንደድህ - መቃጠልህ ምነው?

ናፍቀህ - የናፍቀህ

ብታስብ - ያሰበህ

ብትወድ የወደደህ - ወዳጅ የለምና

ባካኙ ንብረቴ - ልቤ ከእኔው ጽና።

ልብ - ካልከው ልቤ ለልብህ ቁሞ - ነገር

የወርቅ - የዕንቁ ምላሻ ሆኗል ድንጋይ ጠጠር

አዙረህ ወይ ዙረህ - ጥሬ ብ ስሉን ለየው

እከሌን - ከእከሌ - ጥሬ ብስሉን ለየው

ተው ልቤ ተመከር የተውኸን ተወው።

ናፍቀህ - የናፈቀህ

ብታስብ - ያሰበህ

ብትወደ የወደደህ..... ወዳጅ የለምና

ብቸውኛው ጥሬቴ..... ልቤ ከእኔው ጽና

# እንዲህ ኖሯል? (1975 - ተፈጥሮ)

ሰማይ - ምድሩ - ሲመክርበት
ወንዝ - ምንጩ - ሲነጥፍበት
ለምለም - መስኩ - ሲደርቅበት
ውበት - ለዛው - ሲረግፍበት
ቀን - ሲከፋ - ቀን ሲጨቅን
ቀን - ሲጦልግ - ቀን ሲመክን
　　የቁም ሕይወት ልሳነ - ቃል
　　እንዲህ ኖሯል - የሰው - አካል?
ሀገር - ከሀገር - ሲነካ
ሰው እንዲህ - ኖሯል ለካ?
　　ከሚገለው - ሞት - ሲጋደል
　　ከሕይወት - ኑሮ - ድር - ሲታገል\
　　አዋይ - ገበናው - ሲ'ደፋ
　　ቀየ - መንደሩ - ሲ'ከፋ
　　የጐበዝ - ክንዱ - ሲደክም
　　ተፈጥሮ - በሃገር - ሲለግም
　　ጣረ - ሞት - በሕይወት - ሲያገግም
　　ሀገር - ግኘቱ - ሲነካ

ሰው ይህን ይመስላል ለካ?
አንጀት ነክሶ - አንጀት ሲያልም
ሕይወት ጥሎ - ሕይወት ሲያ'ልም
አቅለ - ጉልበቱን ሲሰውረው
ሞቱን እንኳን ሲያነውረው
ለካ ሰው እንደዚህ ነው?
ከመስከ ውለው - ጓሮ - ዞረው
እሸት - በዓይነት - ቀነጣጥሰው
ቃሪያ - ጐመን - ድንች ምሰው
ጠላ - ጠጁን - ወተት ንጠው
አይብ - እርጐ - ቅቤ - አቅልጠው
መሶብ - ሌማት ያስከበሩ
ዘመድ - አዝማድ - ያዘመሩ
የእናት - ጣቶች - ዛሬ - ዝለው
ወርቅ - እጆቿ - ሞትን - አዝለው
ተመካሪ - ተዘካሪ
ዛሬ ሆነው - አይቶ አዳሪ
ከባዶ - ቤት - ሲተያዩ
ከሞት - ሕይወት - ሲወያዩ
እንዲህ ኖሯል የዕጦት ልኩ
የተፈጥሮ - ሕይወት መልኩ?

የሰው - ጠረን - የሰው ትንፋሽ
ጭስ ተነፍጐ - የእህል ንፋሽ
ደረቅ አምባ - ደረቅ አፈር
«እልፍኝ» ሆኖ እና መንደር
ወስከምባዬች - አዋይ - ነጥፈው
በሸረሪት - ድር - ተጠልፈው
አፍላል - ጨጮ - ቅባት ፊድፎ
ጋን - እንስራ - ተንጠፍጥፎ
መሬት - አፈር - አፈር ትቢያ
ትቢያ - ሲሆን - ጥውልግ - ዕሬት
እንዲህ ኖሯል ለካ መልኩ
በየ - ገጹ - በየ - መልኩ?
«የኔ - ቀንበጥ - ለጋው ተክል
እንቡጥ - ፍሬ - የሩቅ ሰብል
የኔ - ሾላ - የኔ ትምቡሽ
የኔ - እምቦሳ - የኔ - ጥንቅሽ
«ብላ» - ማሙሽ - እንድትሰፋ
እንድትወፍር - እንድትፋፋ»
የሚል - ልሳን ክብረ - ማዕረግ
«ማሙሽ» ሳያውቅ «የማሙሽ» ወግ
በልጅ ወጉ - ወተት - ሲያምረው

ከአድማስ - ወዲያ - ርቆ - ሲያየው
የእምዬ ክንድ - ሲዝልበት
የአንጀት ፍቅሯ - ቢደርቅበት
የጡት ስንቋ - ቢነፍጥበት
«ውሃ» እያለ - የሚ'ጠጣ
«እህል» ብሎ - ጥሬ - ቢያጣ
ቀበጥበጣው - ፍልቅልቁ
«ዝም» - ክርትት - ሆኖ ስንቁ
አፍላ ወዙ - ተሸፍኖ
አንደበቱ - ተለስኖ
«ዝም» - ክርትት - ሆኖ ስንቁ
አፍላ ወዙ - ተሸፍኖ
አንደበቱ - ተለስኖ
«ዝም» - ብቻ «ማየት» - ብቻ - ሆኖ አቅሙ
ጉድጓድ - ሆኖ የኑቁ - ሕልሙ
እንደ ሰንጋ - ወርቅ ጥሪት
እንደ - ጋሻ - መሬት ምሪት
የአባት ውርሱን «ረሃብ» ሲያነሳ
ሕፃን ዲዳው ሞት - ሲያገሳ
ቤት! አገር - ወገን - ምንትል
«ማሙሽ» እንኳ ረሃብ ሲስል?

የጐበዝ እጅ - የጐበዝ ክንድ
ስንቱን ቋጥኝ ገፍቶ እሚንድ
ብረት ገላው - ጀግናው ሲዝል
ሸልብ ብሉ - ስልብ ሲል
ዛሬ ሞቶ - ዛሬ በቅቶ
ሞፈር ቀንበር ድር - አድርቶ
በቀን - ምሽት - በቀን ዕጣ
ጋጣ - ብረት ጠረን - ሲያጣ
ማሳ - መከኖ፤ ጥገት - ሲነጥፍ
ማልዶ ወጥቶ - ማልዶ ሲረግፍ
በሕይወት ላይ ሕይወት ሲያድም
እንዲህ ኖሯል የቁም - አቅም?
ግቻ - ነቅሎ - አፈር ምሶ
ቋጥኝ - ነክሶ አገር ክሶ
ዓይነት - በዓይነት - «ባ'ሰፍረው»
ስንዴ - ማኛ «ባስገበረው»
ጐተራውን - ባኮራበት
ፍልሚያ - ገጥሞ በጣለበት
እምቧ! ብሎ - ባጓራበት
«የኔ» ባለው - በመስኩ ላይ
«ዳለች» ወድቆ - ቀርቶ ሲታይ

እንዲህ ኖሯል ለካ መልኩ
የኒ - ዳማ - ውሎ ልኩ?
«መቻል» እንኳ «መቻል» ታክቶት
የቤት - ልምዱ ቁራሽ ናፍቆት
ዛሬ - በቅትቶ - ተሸንፎ
ደፍ - በራፉን - ደጁን አቅፎ
የዕምነት ልቡን - እንዳዘለ
ከጌታው በር ቅርት አለ።
ለካ.....
ቋጥኝ - ካልገፋ ካልማሰነ
ወንዝ - ጅረቱን - ካልለሰነ
ተባይ - አረሙን - ካልነቀለ
አፈር - ካልማሰ - ካልቆለለ
ክንዱ - ለትግል - ካላመፀ
አዕምሮው - ጥበብ - ካላነፀ
ተፈጥሮ - በድል - ካልተገራ
ታሪክ - በሕጉ - ካልተመራ
የሰው - ልጆች - ሕይወት - ስቃይ
«እንዲህ - ኖሯል» ለካ ሲታይ?

..........

..........................

..............................................

# ቁርጥ አቋም ነው (1978 - ግልጽነት)

ጥሉ ጥል ሆኖ ላያስቀይም
ፍቅሩ ፍቅር ሆኖ ጥሞ ላይጥም
ከእንዲህ ዓይነቱ ምራን ጣ
መወዳጀቱን ምን አመጣ?
ከእንግዲህ ዓይነቱ መሰሪ.....
.......ከእንዲህ ዓይነቱ መናፍስት
ጊዜ ጠብቆ ከሚ'ጠጋ......
......ጊዜ ጠብቆ ከሚሸሽ እስስት
እሩቅ ለእሩቅ....... ነው የሚበጅ
ቁርጥ አቋም ነው የሚወዳጅ።
ክንዱ - ክንድ ሆኖ ሊያመካ
ቁም - ነገሩ - በግብር ላይለካ
ሳቁ - ሳቅ ሆኖ ላያረካ
ከድብቅ ዓመሉ ስለት መጋዝ
ማን በምን ተዳው ይጋዝ?
ከአጋም እሾክ ቆንጥር ቀጋ

ማን በምን ተዳው ይጠጋ?

ከእንዲህ ዓይነቱ የመርዝ ብልቃጥ

የማነ ፍቅር በጥል ይዋጥ?

የማነ ዕውነት በሽፍጥ ይዳጥ?

ጉበዝ.....

ከእንዲህ ዓይነቱ አጉል ውላጅ

እሩቅ...... ለሩቅ ነው የሚበጅ

ቁርጥ አቋም ነው የሚያወዳጅ።

........

..........................

.............................................

## ሞስኮቫ (1975 - እንግድነት)

ተርታ - መስመሬን - ሳልለቅ

ረቂቅ የውበት ልስቅ

ፀጋ - እውድታሽን ሣደንቅ

በእምነት «ልቤ» - «ልብ» እንድልሽ

አየህ «ቶባሪሽ» ቢለኝ «ቶባሪሽ»

ሕሊናዬ አካትቼ
ዓይኔን ከዓይኑ አጣክቼ
ሣየው..... ሲያየኝ
ሣተኩረው...... ሲያተኩረኝ

በሩቅ ሕይወት በአሁን አምባ
በአፍላ ስሜት ቁጭት እንባ
በደስታ....
በትዝታ.....
የሩቅ ታሪክሽን ድር አስይዞ - ጉስቁል ሕይወትሽን ሲያስናኝኝ
ዓይነ - ሕሊናዬን ወዲያ ልኮ - ጥንተ - ገበናሽን ሲያሰቃኘኝ
የአመጽ ክንድሽን ፍላፃ - ዝክረ ፍልሚያሽን ሲያስዳስሰሽ
«የደም - ሰንበት» የሃገር እንባ - ትውስታሽን ሲያስተውሰኝ
«የሃያ - ሚሊዬን» ምሙታንሽን - ሕያው መዘክር ሲያጨብጠኝ

ቀና - ብሎ ሲያተኩረኝ - ቀና ብዬ «ሣተኩረው»
«ልብ!» ሲለኝ «ልብ» ስለው

«በዚች ምድር በዚች አገር
የምናየው መልካም ነገር
ዕድገትና ድንቅ ውበቱ
የጀግና ደም አጥንት ነው...... የዘላለም መሠረቱ
እና..... «ቶባሪሽ» ይኸውልሽ..... «ሞስኮቫ» እንዲያ...... ነበረች
በችግር በኩረ ልጆቿ...... ዛሬ ይኸው እንዲህ..... ሆነች»

ብሎ...... ሲለኝ......
ሣተኩረው...... ሲያተኩረኝ
ለአንድ አፍታ ለደቂቃ
በውስጥ ሕይወት ሚስጢር ሲቃ
እኔን - በኔ ቆም አድርጌ......
አንዱን ካንዱ ሣስቲያየው
በጭንቅ ቀን በሩቅ ስሜት.....
ሂደትሽን ሳስታውሰው
አንዳች ነገር ጠቅ! አድርጐ......
ሕሊናዬን አላወሰው።
አዎ......
ታሪክ በታሪክ ሣነፃፅር......
ይህን ይዤ ያን ስተወው
ትግልሽን ለድልሽ ትቼ......
ግኝትሽን በአካል ሣስሰው
በደስታሽ ደስ! ብሎኝ......
ውበትሽን ዛሬ ሳየው
የጥቁር አገር - ጥቁር «አፈር»......
የእህል ልቤን ቀሰቀሰው።
ምስክሻ!
የእምቢኝ እሳት - ሞተር እንዝርት

የአዲስ ሕየት - ሥርዓት እምብርት
የአንዲት እውነት - የአንድ ዓላማ
የእልፍ አዕላፍ - አንድ ማማ
የሠላም ሰንደቅ - ዕምነት ሚዛን
የብዙ ቋንቋ - አንድ ልሣን
መሆንሽን - አየሁ ቆሜ
ልቤን በልብሽ አክስምሜ»
ሞስኮቫ!

ከሚሊዮንም ሚሊዮን ሕዝብሽ ከአገርም አገር ሰማይ
ከኮከብም ደማቅ ኮከብ ከፀሐይም ብሩህ ፀሐይ
በሁለንተናሽ ሰፍኖ ሲታይ
«ደስ» ብሎት «ደስ» ሲያሰኝ መስክሽ በአበባ ፈክቶ
በደም ግኝት ሕይወትን ረክቶ
«ኬላሽ» በጀግናሽ ኮርቶ
«ዜጋሽ» በዓላማው ፀንቶ
ሕልውናው በደሙ ፀድቶ
ተፈጥሮን በትግል ገርቶ

እንዳሻው - እንደልፋቱ
እንዳላማው - እንደምኞቱ
ምሮቱን አንዳች ሣያጣ - ሁሌ ፍስሃ ደጅ ቤቱ
ብራ!...... ዘመን - ፀአዳ ሽቱ

ወንድ ከሴት ሴት ከወንዱ
በአንድ ስሜት በአንድ ክንዱ
ቀና ደፋ - ደፋ - ቀና
የእርሱ ሕይወት «ሥራ» ሁና
የሃገር ፍቅር ቅን ማህተሙ
የአንድነቱ ደም ቀለሙ
ዓላማው ግብ ውሎ ስሌት - የቀን ተሌት ቋንቋ ግሱ
ለሰው ልጆች መልካም ኑሮ - ሠላም! - ሠላም! - መተንፈሱ
ሆኖ ሣየው - አተኩሬ
«ወች - ጉድ!» ብዬ ከማድነቅ ከውበት ማማሽ ተገትሬ
ባየው..... ባይሽ...... ባየው..... ባይሽ
መች ጠግቤው...... መች ጠግቤሽ?
ቃሌን በቃል አካትቼ
ሁሉን ነገር ሁሉን ትቼ
ለደም ግኝት ለውበትሽ
ለዓላማሽ ግብ ለጽናትሽ
ላንቺ ያለኝ ልዩ ስሜት - ለጀግኖችሽ ክብር አካል
የአድናቆቴ ሰርፀት - ቃል
እሰይ!...... ጉሮ ወሸባ......! ጉሮ ወሸባ! ምስክሻ!
ከራሲሻ!...... ብቻ ነው ቋንቋዬ - ከራሲሻ! ከራሲሻ!!
ሞስክሻ!!.....

ዓላማዬን ከዓላማሽ ድር እክድል ግብሽ አጐዳኝተሽ
ሕሊናዬን ከሕሊናሽ የዕምነት ልቤን አጠንጥነሽ
«ጉልበትህን - ካልሰሰትከው
ዕውቀትህን - ካልሸሸከው
ሃቅ ዕውነትን - ካልሸፈጥከው
ህይወትህን ለዓላማህ ግብ - ለምኞትህ ካልነፈከው
የአንተንም ጉዞ መጠበቁ ግኘት ድሉ ግቡ ይህ ነው
አይዞህ ታገል! ደም ሕይወት ስጥ.......
......ቁርጠኛ ሁን ቅን መልካም ሰው»
ያለኝ ቃልሽ ስንቅ ይሁነኝ
ዛሬ ነገን እንዲያሳየኝ
ሞስክቫ!!......
ላክብሮተሽ - እስፓሲቫ
ለውበትሽ - ክራሲቫ
ዶሲዳንያ!...... ሞስክቫ..... ዶሲዳንያ!» አህታችን
እሩቅ አይሁን - መተያያችን
እሩቅ አይሁን - መነፃፀሪያችን።
ሞስኮ 1975

........

..............................

............................................

# ቃል - ገባሁልሽ (1976 - የመጨረሻ ቃል)

«ይከስከስ እንጂ አጥንቴ ይብነን እንጂ እንደ አቧራ
ይቆረጥ እንጂ ስጋዬ ይመተር እንጂ በካራ
እናት ሃገር እናት ዓለም
ጥቃትሽን ቆሜ - አላይም»
ብዬ.....
ቃል ገባሁልሽ ሃገሬ
የማህፀንሽ ግኝት ፍሬ።
«ሲነገር ሲከበር የኖረው የዘመናት ሕያው ታሪክሽ
የአንድነትሽ ጽኑ ዋልታ የነፃነት መንበር ክብርሽ
የአዲስ ሕይወት መስተንግዶ የዓለም ሰላም ሰንሰለትሽ
በቅን መድረክ ፍልሚያ ውሎ - በልጅሽም ደም ፍሳሽ ወኔ
ይጠበቃል እናት በእኔ።
ግፍና ጭቆና እንግልቱ - የስቃይ ብሶት እሮሮ
የጐሣ..... የዘር..... ሽንሽኖሽ - የላይ የታች ብኩን ኑሮ
ከእንግዲህ ላይኖር በምድርሽ
ደም - ሕይወቴ ይኸውልሽ።»
ብዬ.....
ቃል ገባሁልሽ ይኸውና በአገር ምድር በአገር ሰማይ

ጥቃትሽን ቆሜ ላላይ።

«የጀግኖችሽ ክብር አጽም የዓላማቸው ሀቅ ምስሉ
የትውልድ ታሪክ ውርስ የአደራ ብያኔ ቃሉ
ስለ ደረሰኝ ለኔም ውሉ
እናት ዓለም እኔም ልጅሽ
የማህጸንሽ ግኝት ምስልሽ
የነፃነት ዓርማ ምልክት
ለጥቃትሽ ሆኜ ምትክ
ምትሽን እኔ ልመታ ሞትሽን ቀድሜ ልሙት
ለሚቃጣብኝ የጦር መዘዝ ለዕብሪተኞች ስንዛሬ
የጥይት መከተቻ ዝናር ጋሻ ይሁንሽ ግንባሬ!»
ብዬ.......
ቃል ገባሁልሽ ይኸው ቃሌ
ድልሽ እኒ ሽንፈትሽ - ዕድገትሽ እንጂ ውድቀትሽ..... ላይሆን ውሌ።
የእናት ምድሬን አፈር ይዤ አፈር ትቢያ ልሆንልሽ
ይኸውና ቃል ገባሁኝ በወንዞችሽ ምድር ሰማይ
ከድል በፊት ፊቴ ላይዞር...... የሚያየኝን ወገን ላላይ!»
ብዬ.....
ቃል ገባሁልሽ ሃገሬ
የማህፀንሽ ግኝት ፍሬ

# ምስጋና

ለጅምር ሥራዬ ተግባራዊ ዕይታ መድረስ ከፍተኛ ዕርዳታ ላደረገልኝ ለአብዮታዊ ጦር ኃይሎች ዋና ፖለቲካ አስተዳደር......

የሃሣብና የማቴሪያል ድጋፍ ለለገሱኝ ለጓድ ሻምበል ጀንበሬ ተሰማ ለጓድ አያልነህ ሙላት ለጓድ፥ሻምበል እሸቱ ቱፋ.....

ለህትመቱ ጥራትና መፋጠን ከተገቢው በላይ ከፍተኛ ጥረት ላደረጉልኝ ለቦሌ ማተሚያ ቤት ሠራተኞች ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ሻለቃ ክፍሌ አቦቸር ለግጥም የተፈጠሩ ሰው ናቸው ሲሉ ይናገራሉ በስራቸው የሚያውቋቸው ሁሉ ። እስከዛሬም ዘልቀው የምናደምጣቸው ተወዳጅ ሀገራዊ የዘፈን ግጥሞችን ጽፈዋል ። አራት የግጥም መጽሐፍቶችንም ለህትመት አብቅተዋል ፤ ከዚህም ውጪ ህዝባዊ መዝሙሮችንም በመድረስ ይታወቃሉ ሻለቃ ክፍሌ አቦቸር ።

። ሻለቃ ክፍሌ አቦቸር ከስነ-ጽሑፍ ባለሞያነታቸው ውጪም አርበኛም ጭምር ናቸው ።

የቀድሞው የሆለታ ጦር አካዳሚ ምሩቅ እና በሱማሌ ጦርነት ጊዜ በታጠቅ ጦር ሰፈር ስልጠና ይወስድ የነበረውን የሚሊሻ ጦር በፓለቲካ ከማንቃት ጀምሮ እስከ ጦርነቱ ድረስ የተሳታፉ የቀድሞ የኢትዮጲያ ጦር ሰራዊት አባል የነበሩ እንዲሁም በጦርነቱም ጊዜ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸው እንደሌሎች ውድ ኢትዮጲያዊያን ጓዶቻቸው ሁሉ ለሀገራቸው መስዋትነትን በመክፈል ለሀገራቸው ያላቸውን ጥልቅ ፍቅር ከጥበብ ውጪ ህይወትን ለመክፈል በመወሰን ጭምር ያሳዩ ድንቅ ኢትዮጲያዊም ናቸው ። የሀገር ፍቅር ፣ ሰላም ፣ ህብረት ፣ አንድነት ፣ መተባበር ፣ ጀግንነት ፣ ሉዓላዊነት ፣ ነጻነት አጠቃላይ ኢትዮጲያና ኢትዮጲያዊነትን የሚያጎሉ አበይት ነጥቦች የግጥሞቻቸው ማዕከላዊ ማጠንጠኛዎች ናቸው ።

## የደራሲው ሥራዎች

1. የኔ ጋሻ (ግጥምና ቅኔ)
2. አንድ ቀን (ግጥምና ቅኔ)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY